የመጋዘን ሰራተኞች መመሪያ

የሰብአዊ ዕርዳታ እና ሴፍቲኔት ፕሮግራም



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የመጀመሪያ ዕትም-ህዳር 2007/November 2014
(ዕትም 1.0)

በዚህ አነስተኛ የመጋዘን ሰራተኞች መመሪያ የሚገኙት መረጃዎች የተወሰዱት አ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ በ2007 ዓ.ም ካዘጋጀው ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የዕርዳታ ቁሳቁሶች አስተዳደር ማንዋል ነው።።

በመፅሐፉ ውስጥ ከገፅ 17 – 22፣ 27 – 37፣ 64-68 እና ከ86-89 የሚገኙት ሥዕላዊ መግለጫዎች ከአለም የምግብ ፕሮግራም በፍቃድ በድጋሚ የታተሙ ናቸዉ።።

ይህ አነስተኛ የመጋዘን ሠራተኞች መመሪያ የመንግስት ሰነድ ስለሆነ ከወረዳ አስተዳደር ይህን ማንዋል ስትቀበሉና ከስራ ስትሰናበቱ በማስረከብ መፈረም ይጠበቅባችኋል።። ይህም የታተሙ ቅጅዎች አላግባብ እንዳይጠፉና ሠራተኞች ለወደፊት የሚሻሻለውን መመሪያ በወቅቱ ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ ነው።። ሠራተኛው መ/ቤቱን በሚለቅበት ጊዜ ኃላፊው መመሪያውን ስለመመለሱ ፊርማውን በማኖር ማረጋገጥ አለበት።።

መግቢያ

ይህ *መመሪያ* የሚያተኩረው የመጋዘን ሰራተኞች ወረዳቸውን በመወከል የዕለት ዕርዳታን እና/ወይም የልማታዊ ሴፍቲኔት ቁሳቁሶችን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ነው። እነዚህ የእርዳታ ቁሳቁሶች የሚጓዝዙት በተፈጥሮ አደጋ ለተጎዱ ሰዎች እና ስር የሰደደ የምግብ ዕጥረት ላለባቸው (ማለትም የምግብ ፍላጎታቸውን በዝናብ ወቅት ሳይቀር በማምረትም ሆነ በመሸመት በበቂ ሁኔታ ማሟላት ለማይችሉት) ነው።

የእርዳታ ቁሳቁሱ በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል በማድረግ በተረጂዎች ህይወት ላይ ብሎም በኢትዮጵያ ላይ ለውጥ የማምጣት ሚናችሁ በግለሰብ ደረጃም ሆነ በአጠቃላይ የላቀ ነው። የእርዳታ ቁሳቁሶቹ በእናንተ ቁጥጥር ስር እያሉ ቢጠፉ፣ ቢሰረቁ፣ወይም ቢበላሹ ለእያንዳንዱ ተረጂ የሚደርስ በቂ ምግብ ስለማይኖር ዕርዳታዉን ያላገኙቱ ሊራቡ የግድ ይላል። የሚበሉት ባለማግኘታቸው ምክንያት ለህመም እንዲጋለጡ ወይም ያላቸውን ጥሪት እንዲሸጡ ይገደዳሉ። ስለሆነም *መንግስት* የእነዚህን ሰዎች ጥሪት ለመገንባትና ከድህነት እንዲላቀቁ የሚያደርገውን ጥረት ሊያዳክም ይችላል።

በዚህ ምክንያት ከዕርዳታ ቁሳቁሶች በተጨማሪ የእናንተን የሪፖርት አጠነቃቀርና *መረጃ* አያያዝ ሁኔታ በጣም ወሳኝነት አለው። የፌዴራል *መንግስት* እጅግ አስፈላጊነቱን በመረዳት ስራችሁ የተቀላጠፈ እንዲሆን ይህን የመጋዘን ሰራተኞች *መመሪያ* እና ቅጅ ያላቸውን ሪፖርት ማጠናቀሪያ ጥራዞችን ከፍተኛ ወጪ በማውጣት አዘጋጅቷል።

ሪፖርት ማጠናቀሪያ ጥራዞችንና ሌሎች በስርጭት ጣቢያዎች እንድትገለገሉባቸው በመንግስት የተፈቀዱ ቅጾችን መጠቀም በጣም አስፈላጊ ነው። ተሻሽለው የወጡትን አዳዲሶቹን ቅጾች እና ፎርሞች በመመሪያዉ የዉስጥ ሽፋን ኪስ ዉስጥ በካርድ ቁ 1 ላይ ይገኛሉ።

ዓላማዉ

ይህ የመጋዘን ሰራተኞች *መመሪያ* በስርጭት ጣቢያ የሚገኙ የእርዳታ ቁሳቁሶችን አያያዝና የመጋዘን አጠቃቀም *መ*ልካም ተሞክሮዎችን የሚያስረዳ ነው። በተጨማሪም *መንግስት* የእርዳታ ቁሳቁሶችን በአጠቃላይ በተገቢው *መንገ*ድ ለማስተዳደር እንዲያስችለው የሚያግዝ ስለ ሪፖርት አጠነቃቀርና *መረጃ* አያያዝ ያካተተ ነው።

የተፈጻሚነት ደረጃ

የአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የእርዳታ ቁሳቁሶች

ከማንኛውም ለጋሽ የተገኙ ቢሆንም ወይም የለጋሹ ስም በማሸጊያው ላይ ቢኖርም ይህ የመጋዘን ሰራተኞች መመሪያ ተፈፃሚነት የሚኖረው በአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ በኩል ለተቀበልናቸዉ የእርዳታ ቁሳቁሶች ብቻ ነው።።

ከፈዴራል መንግስት አስቀድሞ በተገኘ ይሁንታና ስምምነት መሰረት የዕለት እርዳታንና የሴፍቲኔት የእርዳታ ቁሳቁሶችን ከዓለም ምግብ ፕሮግራም ወይም መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ማግኘት ይቻላል።። አንዳንድ ጊዜ የዓለም ምግብ ፕሮግራም ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በቀጥታ የሚሳተፉ ከሆነ የዕርዳታ ቁሳቁሱን ለመረከብ፣ለማከማቸትና ለማከፋፈል የራሳቸውን አሰራር መከተል ይችላሉ።። ነገር ግን በዚህ ተግባር የተሳተፈ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅትም ሆነ የዓለም ምግብ ፕሮግራም ለሚመለከተው የወረዳ መስተዳደር በተናጠል ሪፖረት ማቅረብ ይኖርበታል።። መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የዓለም ምግብ ፕሮግራም ሪፖርት አጠነቃቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ አልተካተተም።።

የዕለት እርዳታ እና የሴፍቲኔት የእርዳታ ቁሳቁሶች

ይህ መመሪያ ተፈጻሚነት የሚኖረው በዕለት እርዳታ እና በሴፍቲኔት የእርዳታ ቁሳቁሶች ብቻ ላይ ነው።።

እንደ መጋዘን ሰራተኛነታችሁ የምትረከቡት የእርዳታ ቁሳቁስ ለየትኛው ፕሮግራም እንደሆነ ማወቅ ይኖርባችኋል።። ይህ በጣም አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት የእርዳታ ቁሳቁሶቹ በየፕሮግራሙ አይነት ለየብቻቸው በመደርደር የተናጠል ምዝገባና ሪፖርት ማድረግ ስለሚያስፈልግ ነው።። ቁሳቁሶቹ እንዲሰራጩ ወረዳው ትዕዛዝ ሲያስተላልፍ አግባብ ለሆነው ፕሮግራም ትክክለኛውን የዕርዳታ ቁሳቁስ መላክ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።። በአንድ የስርጭት ጣቢያ መጋዘን ውስጥ በተመሳሳይ ጊዜ ከአንድ በላይ ለሆኑ ፕሮግራሞች የእርዳታ ቁሳቁስ በሚራገፍበት ወቅት ይህን አይነቱን አሰራር መተግበር ጠቃሚ ነው።።.

በአስቸኳይ የሚሰራጩ የእርዳታ ቁሳቁሶች

የእርዳታ ቁሳቁሶችን ለማሰራጨት መንግስት ባስቀመጠዉ አስገዳጅ የጊዜ ገደብ መሠረት ይህ መመሪያ የእርዳታ ቁሳቁሶች በማሰራጫ ጣቢያ መጋዘን የሚቆዩበትን ጊዜ ከግምት ውስጥ ያስገባል።። የተሻሻለው አስገዳጅ የጊዜ ገደብ ከመመሪያዉ ጋር አባሪ ተደርጎ በካርድ ቁ 2 ላይ ይገኛል።።

አስቀድሞ ለተንዝዘ የእርዳታ ቁሳቁስ /pre - position/ ግን የተለየ አሰራር ወይም በመጋዘን ውስጥ ለረዥም ጊዜ የሚቆዩበት ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል ከዚህ መመሪያ አሰራር ውጪ ነው።።

ልዩ ምልክቶች



መረጃው በጣም ጠቃሚ መሆኑን ያመለክታል



በዚህ መመሪያ ውስጥ የሚገኘውን ባለቁጥር ካርድ ያመላክታል (ለምሳሌ ካርድ ቁ. 1)።። ካርዶቹ እንድትገለገሉባቸዉ የሚያስፈልጉ አስገዳጅ ቅጾችን እና በወቅቱ እንድታጠናቅቁ የሚያስገድዱ የጊዜ ገደቦችን እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን የያዙ ስለሆነ እጅግ አስፈላጊ ናቸዉ።። በካርዶቹ ላይ የሚገኙት መረጃዎች ወቅታዊነታቸዉ እንዲጠበቅና በየጊዜው ማሻሻል እንዲቻል (እንደ አስፈላጊነታቸው ቅደም ተከተል) ከመመሪያዉ ዉጭ ለብቻ እንዲቀመጡ ተደርገዋል።። ለምሳሌ ለወደፊት የአሰራር ቅልጥፍና በሚሻሻልበት ወቅት የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሊያጥር ይችላል ፤ ስለሆነም የተሻሻለውን የጊዜ ገደብ ለመጋዘን ሰራተኛው ለማሳወቅ እንዲቻል አዲስ ካርድ ይዘጋጃል።።

ካርዶቹ በተደጋጋሚ በመመሪያዉ ውስጥ ሊጠቀሱ ስለሚችሉ በታተሙበት ቀን እና ቁጥር በቀላሉ መለየት ይቻላል።። በዚህ ማንዋል ውስጥ ከሚገኙት ካርድ ቁ. 1 - ቁ. 4 በመሀል የጠፉ ካሉ በአስቸኳይ ለቅርብ ሀላፊ በማሳወቅ ካርዶቹን መተካት ይቻላል።። የመጀመሪያው መመሪያ ከታተመ በኋላ የተሻሻሉ ካርዶች ወይም አዲስ ካርድ የታተመ ከሆነ የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል።።



የምትገለገሉባቸውን አስገዳጅ ቅጾች ያመለክታል።። እነዚህ ቅጾች ካልደረሱዋችሁ በስቸኳይ ለቅርብ ኃላፊ በማሳወቅ ማግኘት ይኖርባችኋል።። የተሻሻሉ አስገዳጅ ቅጾችን በመመሪያ ውስጥ ተካትተው በአዲሱ ካርድ ቁ. 1 ውስጥ ይገኛሉ።።


የመጋዘን ሰራተኞች መመሪያ አጠቃቀም

ይህ መመሪያ አንድ የመጋዘን ሰራተኛ የዕለት ተዕለት ተግባሩን ታሳቢ በማድረግ በሰምንት ክፍሎች ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ነው።።

- **ክፍል** 1 የሚጠበቁባችሁን ስራዎችና በአጠቃላይ ከዕለት እርዳታ እና ከሴፍቲኔት ፕሮግራም አንጻር ያሉባችሁን ሀላፊነቶች በዝርዝር ያስቀምጣል።።

- **ክፍል** 2 - **ክፍል** 6 የእርዳታ ቁሳቁሶችን ለመረከብ በምትዘጋጁበት ፣ በምትረከቡበት ፣ በምታከፋፍሉበት ወቅቶች እና ወርሃዊ ሪፖረት አጠናቅራችሁ በምትልኩበት ወቅት እንዲሁም በመጋዘን የተከማቹ ቁሳቁሶችን ሳምንታዊ ፍተሻ በምታከናውኑበት ወቅት መከተል የሚኖርባችሁን ዝርዝር ስራዎችን ያካተቱ ናቸው።። ከዚህ በታች በሚገኘው ስዕላዊ መግለጫ ተዘርዝረው ይገኛሉ።።

ምስል 1፡ የዕለት እርዳታ እና የሴፍቲኔት ፕሮግራም የእርዳታ ቁሳቁሶች አያያዝ ዋና ዋና ተግባራት




እያንዳንዱ ዝርዝር ስራ በቁጥር በተደለደለ ደረጃ ተከፋፍሎ ይገኛል።። እያንዳንዱ ክፍል የሚጀምረው በዛ ክፍል ዉስጥ የተቀመጡትን ዝርዝር ስራዎች በስዕላዊ መግለጫ ሂደታቸውን በማሳየት ነው።። ጎን ለጎን የተቀመጡ ሂደቶች/ደረጃዎች ሁሉንም በአንድ ጊዜ ማከናወን እንደሚቻል የሚያሳይ ነው።።

ከታች የተቀመጠ ሂደት/ደረጃ ከሆነ ግን የላኛውን ሂደት አስቀድማችሁ ማከናወን ይጠበቅባችኋል።።

ለምሳሌ የሚከተለው ስዕላዊ መግለጫ ስለ ቁሳቁስ አደራደር ከማቀዳችሁ በፊት መጋዘኑን ማጽዳት እንዳለባችሁ የሚያስረዳ ቢሆንም ወዛደሮቹን በተመሳሳይ ጊዜ በማሳወቅ ጽዳቱን መቀጠል እንደምትችሉ ያስረዳል።።

ምስል 2፡ ለመረከብ መዘጋጀት የስራ ሂደት ምሳሌ



የእናንተ የስራ ኃላፊነት ያልሆኑ ነገር ግን ስራችሁን ለማከናወን አስቀድሞ የሌሎች ክፍሎች ተግባራት መከናወን አስፈላጊ ከሆነ (ወይም ስለ ስራቸው ሁኔታ አስቀድማችሁ ማወቅ ካለባችሁ) ይህን ሁኔታ ለማሳየት ቀስቶችን እንጂ በቁጥር የተዘረዘሩ ደረጃዎች አልተጠቀምንም።።

ከዚህ በታች በሰንጠረዡ ላይ እንደሚታየው የሚቀጥሉትን ተግባራት ለማከናወን የቀስቶቹ አቅጣጫ በእነርሱ ስራ ላይ ጥገኛ መሆናችሁን ወይም እነርሱ በእናንተ ስራ ላይ ጥገኛ መሆናቸውን ያሳያሉ።።

የቀስቱ አቅጣጫ	ትርጓሜ	ምሳሌ
	ስራችሁን ለማጠናቀቅ አስቀድሞ መጠናቀቅ ያለበት ተግባርን ያመላክታል	የእርዳታ ቁሳቁስ መላኩን መረጃ መቀበል (ጭነቱ እየደረሰ እንደሆነ በማወቃችሁ መጋዘኑን ማጽዳትና ወዛደሮቹን ማሳወቅ ትችላላችሁ)
	ይህ ተግባር እንዲከናወን የእናንተ ስራ አስቀድሞ መጠናቀቅ እንዳለበት ያመላክታል	የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ ሪፖርት መላክ (የወረዳውን ወርሃዊ ሪፖርት ለማጠናቀር ከእናንተ የሚመጣ ሪፖርት በጣም አስፈላጊ ነው)
	በቀጥታ የእናንተ ኃላፊነት ባይሆንም ይህ ስራ እንደሚከናወን ማወቅ ይኖርባችኋል	ለወዛደሮቹ አሽከርካሪው መክፈል ይኖርበታል

- **ክፍል** 7 እንደ መጋዘን ሰራተኛነታችሁ የዘወትር ተግባራችሁን ለማከናወን ማወቅ ስላለባችሁ ነገሮች የሚያስረዳ ክፍል ነው፤ ለምሳሌ መሰረታዊ የመጋዘን ጥገና እንዴት መከናወን እንዳለበት፣ የመጋዘኑን የመያዝ አቅም ማስላት እንዴት እንደሚቻል፣ ምን ምን አይነት መገልገያዎች በአቅራቢያችሁ መኖር እንዳለባቸዉ እና የመሳሰሉት፡፡

- **ክፍል** 8 በዚህ መመሪያ አግባብ መሰረት የቃላት ፍቺዎችን የሚጠቅስ ክፍል ነው፡፡

እያንዳንዱ ክፍል በሚቀጥለው ገጽ ላይ ጠቅለል ባለ ሁኔታ የተገለጸ ሲሆን እንደ ማውጫም ያገለግላል፡፡ በእያንዳንዱ ገጽ ጠርዝ ላይ የሚታዩት ምልክቶች ወደ ተለያዩ ምዕራፎች በቀላሉ ለማጣቀስ የሚረዱ ናቸው፡፡



የመጋዘን ሠራተኛው ሚና

ከሴፍቲኔት እና ከዕለት እርዳታ ፕሮግራም ጋር በተያያዘ የሚኖራችሁን ሚና እና ኃላፊነት የሚያስረዳ ነው



ለመረከብ መዘጋጀት

የእርዳታ ቁሳቁሶች በመንገድ ላይ መሆናቸውን እንደተነገራችሁ ዘወትር መከተል የሚገባችሁን አሰራሮች የሚያስረዳ ነው



የእርዳታ ቁሳቁሶችን መረከብ

በስርጭት ጣቢያ መጋዘን የእርዳታ ቁሳቁሶችን በምትረከቡበት ወቅት መከተል የሚኖርባችሁን አሰራሮች የሚያስረዳ ነው



የእርዳታ ቁሳቁሶችን ማሰራጨት

ለተፈቀደለት የእርዳታ ቁሳቁስ አከፋፋይ ከስርጭት መጋዘን አውጥታችሁ በምታሰተላልፉበት ወቅት መከተል የሚገባችሁን አሰራር የሚያስረዳ ነው



ወርሃዊ ሪፖርት

በወሩ ውስጥ የተረከባችሁትን፣ ያከማቻችሁትን እና/ወይም ወጪ የሆነዉን የእርዳታ ቁሳቁስ ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን እንዴት ሪፖርት ማጠናቀር እንዳለባችሁ የሚያስረዳ ክፍል ነው



ሳምንታዊ የእርዳታ ቁሳቁስ ፍተሻ

የእርዳታ ቁሳቁስ በመጋዘን ውስጥ ተከማችቶ የሚገኝ ከሆነ ዘወትር በየሳምንቱ እንዴት ፍተሻ ማከናወን እንደሚቻል የሚጠቅስ ክፍል ነው።።



የስርጭት ጣቢያ መጋዘን ከባቢያዊ ሁኔታ


ስለ ስርጭት ጣቢያ መጋዘን አመራረጥና የጥገና ስራ (እንደ መጋዘን ሰራተኛነታችሁ አነስተኛ ጥገናዎችን በራሳችሁ ማከናወን ይኖርባችኋል) እንዲሁም የመጋዘኑን የመያዝ አቅም ማስላት አሰራሮች መመሪያ የሚሰጥ ክፍል ነው።።



የቃላት ትርጉም

በዚህ መመሪያ አግባብ መሰረት የተጠቀሱ ዋና ዋና ቃላቶች ትርጉም የሚገኝበት ክፍል ነው

1



የመጋዘን ሰራተኛ ኃላፊነት

1 የመጋዘን ሰራተኛ ኃላፊነት

እንደ መጋዘን ሰራተኛነታችሁ በወረዳው የሚገኘውን አንድ ወይም ከዚያ በላይ የስርጭት ጣቢያዎችን በሃላፊነት በማስተዳደር በስራችሁ በሚገኙት መጋዘኖች ያሉትን የገቢና የወጪ ዕቃዎች ትቆጣጠራላችሁ፤ የቁሳቁሶቹን ጥራት በመጠበቅ ከብክነት ትከላከላላችሁ፡፡

በተለይም የዕርዳታ ቁሳቁሶች ሲጓዝ፣ ሲጫኑና ሲወርዱ፣ እንዲሁም በመጋዘን በሚከማቹበት ወቅት ብክነት፣ብልሽትና ጉዳት እንዳይደርስ የተሸሻሉ የአያያዝና የክምችት አስተዳደር ልምዶችን በመጠቀም ትከላከላላችሁ፡፡ ይህ መመሪያ ለዚህ አሰራር ጠቃሚና መሰረታዊ የሆኑ መመሪያዎችን አካትቷል፡፡

የመጋዘን ሰራተኛ - ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች አስተዳደርን በተመለከተ ዝርዝር ኃላፊነት ከዚህ በታች ተጠቅሷል፡፡

ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን አስተዳደር በተመለከተ የእናንተ ኃላፊነት

- ✓ የዕርዳታ ቁሳቁሱ ከመድረሱ በፊት የስርጭት ጣቢያ መጋዘን ዝግጁና ፅዱ መሆኑን ታረጋግጣላችሁ፣
- ✓ ወዛደሮችን በማስተባበር የዕርዳታ ቁሳቁሱን እንዲያራግፉና እንዲያከማቹ ማድረግ እና የማራገፍና የማከማቸት ስራው በጥንቃቄ መሆኑን ማረጋገጥ(አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥልጠና ትሰጣላችሁ)፣
- ✓ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን ስለመረከብ
  - ○ ከመራገፋቸው በፊት መመርመርና በሚራገፉበት ወቅት መቁጠር እንዲሁም የተበላሸ ከተገኘ ወዲያውን መለየት፣
  - ○ የመረከቢያ ሰነድ በማዘጋጀት በእያንዳንዱ ዙር የተላኩትን ቁሳቁሶች መለያ ልዩ ቁጥር (የአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የወጪ ሠነድ ቁጥር) በመረከቢያ ሰነድ ላይ መጻፍ ይኖርባችኋል፡፡ በተጨማሪም በጉዞ ወቅት የጠፉ ወይም የተበላሹ ቁሳቁሶች ካጋጠማችሁ በሰነዱ ላይ ማሳወቅ ይኖርባችኋል፡፡
- ✓ እርዳታ ቢዘገይ ወይም ከሚጠበቀው አንሶ ቢደርስ እና በመጋዘን እያለ ቢጠፋ ለቅርብ አለቃችሁ ማሳወቅ ይጠበቅባችኋል፣

- ✓ የእርዳታውን ቁሳቁስ በወረዳው ትዕዛዝ መሰረት ማሰራጨት ይጠበቅባችኋል፡፡ በተጨማሪም በምታሰራጩበት ወቅት የወጪ ሰነድ በማዘጋጀት ቅጅዎቹን ለሚመለከታቸው ማሰራጨት ይኖርባችኋል፡፡
- ✓ የእርዳታ ቁሳቁሶች በመጋዘን ካሉ ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ ደህንነታቸውን መፈተሽ፣
  - ○ ለስርጭት ጣቢያ መጋዘኖች አነስተኛ ጥገናዎችን ማካሄድ/መቆጣጠር፣
  - ○ ከፍተኛ ጥገና ወይም መሳሪያዎች የሚያስፈልጉ ከሆነ ለቅርብ አለቃ ማሳወቅ፣
  - ○ ተባዮችን በመቆጣጠር የእርዳታ ቁሳቁሶችን ደህንነት መጠበቅ፣
  - ○ የስርጭት ጣቢያ መጋዘን እና አካባቢውን ንጽህና መጠበቅ፣
  - ○ ቆሻሻን ማስወገድና (የተበላሹ ምግቦች ካሉ ለቅርብ አለቃ ማሳወቅ)፣
  - ○ የመጋዘን ፍተሻ ሪፖርት በየጊዜው በማጠናቀር በፋይል ማስቀመጥ፣
- ✓ የስርጭት ጣቢያ መጋዘን ደህንነት ምንጊዜም መጠበቅ ፣
- ✓ ሠነዶችን ማዘጋጀት እና መዝገብ መያዝ፡-
  - ○ የስርጭት ጣቢያ መዝገብ ሁልጊዜ መሙላት(በስርጭት ጣቢያ መጋዘን የገባ እና የወጣ ካለ መመዝገብ)
  - ○ በጥንድ/በአንድ ላይ ፋይል ማድረግ፡ 1ኛ) የአደጋ መከላከል ዝግጁነት እና ምግብ ዋስትና ዘርፍ የወጪ ሠነዶችና የመረከቢያ ሠነዶች 2ኛ) የወጪ ትዕዛዞች፣ የዕቃ መጠየቂያና የስርጭት ጣቢያ የወጪ ሠነዶች፡፡
  - ○ ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት፤ በመጋዘን ዉስጥ ያሉ ቁሳቁሶችን ቆጠራ ማካሄድና ሪፖርቶቹን ወደ ወረዳ መላክን ጨምሮ
- ✓ የኦዲት/የቆጠራ/የክትትልና የግምገማ ስራዎችን ማገዝ/መደገፍ፡፡



እንደ መጋዘን ሰራተኛነታችሁ የእርዳታ ቁሳቁሶችን ማሰራጨት አይጠበቅባችሁም፡፡ በመሰረቱ ይህ ስራ ከማህበረሰቡ የተውጣጡ የስርጭት ኮሚቴዎች ኃላፊነት ነው፡፡ በተጨማሪም የስራ ግጭት እንዳይፈጠርና ሙስናን ለመከላከል ወረዳውን በመወከል ስርጭቱን የሚቆጣጠር በየጊዜው የተለያዩ ሰዎችን ወረዳው መመደብ ይኖርበታል፡፡


2



ከማድረስ መዘጋጀት

2 ለማድረስ መዘጋጀት

ምስል 3፣ ለማድረስ መዘጋጀት - የስራ ሂደቶች



የእርዳታ ቁሳቁስ እየተጓዘ መሆኑን ማሳወቅ

እናንተን የሚመለከት የእርዳታ ቁሳቁስ ወደ ማሰራጫ ጣቢያ መጋዘን መች እንደሚደርስ ያሳውቁሃል፡፡ ቁሳቁሶቹ ከአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ ማዕከላዊ መጋዘን መች እንደተላኩ እንዲሁም አይነታቸውንና ጠቅላላ ብዛታቸውን ያጠቃልላል፡፡

የማሰራጫ መጋዘኑን ለማዘጋጀት ፣ ድርድሩን ለማቀድ እና ወዛደሮቹን ለማሳወቅ በአፋጣኝ የሚከተሉትን የአሰራር ደረጃዎች መከተል ይኖርባችኋል፡፡

ደረጃ 1: አስገዳጅ ቅፆችና ፎርሞች መኖራቸውን ታረጋግጣላችሁ

1

የዕርዳታ ቁሳቁሶቹን ከመረከባችሁ በፊት አስቀድማችሁ ቁሳቁሶቹን ለማስተዳደር የሚረዱት አስፈላጊ ሠነዶች መኖራቸውን ማረጋገጥ ይኖርባችኋል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት በየስርጭት ጣቢያ የሚገኙ የመጋዘን ሰራተኞች እንዲጠቀሙባቸው ያጸደቀውን ዋና ዋና የዕርዳታ ቁሳቁስ አስተዳደር ሠነዶችን እንደመሚከተለው በካርድ ቁ. 1 ላይ ተገልጸው ይገኛሉ፡-

የጸደቀት አሰገዳጅ ቅጾች ለወደፊት የሚሻሻሉ ከሆነ በተሻሻለው **ካርድ ቁ.1** ውስጥ የሚካተቱ ሲሆን ትክክለኛ የሆኑትን ቅጾች ስለመጠቀማቸው ሁልጊዜ ካርዱን ማመሳከር ይኖርባችኋል።

- **የመረከቢያ ሠነድ** (በክልሉ መንግስት የሚሰጥ ግልባጭ ያለው ፓድ/ጥራ) ፡- የተወሰነ መጠን ያለውን የዕርዳታ ቁሳቁስ መረከባችሁን ለማረጋገጥ የሚሰጥ ደረሰኝ ነው። በአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ ሰነድ ላይ በተቀመጠው ዝርዝር መሰረት የመረከቢያ ሰነድ በመቁረጥ የእርዳታ ቁሳቁሱን አይነትና መጠን በይፋ መረከባችሁን መግለጫ ነው። ከእርዳታ ቁሳቁሶቹ ጋር ተያይዞ የመጣውን የአ/መ/ዝ/ም/ ዋ/ዘ የወጪ ቁጥር በመመዝገብና የተረከባችሁትን ቁሳቁስ ብዛትና ሁኔታ ከማዕከላዊ መጋዘን ወደ ስርጭት ጣቢያ በሚጓጓዝበት ወቅት የጠፋ ወይም የተጎዳ ቄምር ካለ መመዝገብና መግለጽ ይኖርባችኋል።

- **የስርጭት ጣቢያ የወጪ ሠነድ** (በክልሉ መንግስት የሚሰጥ ግልባጭ ያለው ፓድ/ጥራዝ) ፡- በወጪ ትዕዛዝ እና/ወይም በመጠየቂያ ሠነድ ላይ ወረዳው ባጸደቀው መመሪያ መሰረት ለማሰራጨት ሥልጣን የተሰጠው አካል (ለምሳሌ፥ የቀበሌ ሊ/መንበር) ዕርዳታውን እንዲያከፋፍል የሚሰጥ ሠነድ ነው። ለማሰራጨት ስልጣን ለተሰጠው አካል የስርጭት ጣቢያ የወጪ ሰነድ በመስጠት የተጠቀሱትን የእርዳታ ቁሳቁሶች አይነትና ብዛት በይፋ ማስተላለፋችሁን ያረጋግጣል።

- **የስርጭት ጣቢያ ሌጀር/መዝገብ** (በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰራበት ሌጀር/ መዝገብ)፡- በስርጭት ጣቢያ የሚገኘውን የክምችት ሁኔታ አጠቃላይ ግንዛቤ የሚሰጥ ሲሆን ጣቢያው የተረከበውን፣ያከፋፈለውንና ከወጪ ቀሪ ያለውን የሚያሳይ ሲሆን በተጨማሪም በመጋዘን ውስጥ የጠፋትን/የተበላሹትን ያጠቃልላል።

- **የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የገቢ ሪፖርት** (በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰራበት ግልባጭ ያለው ፓድ/ጥራዝ ነው) ፡- በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር መሰረት ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን ወርሃዊ ሪፖርቱን አጠናቃችሁ በኢትዮጵያዊያን ቀን አቆጣጠር ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን ለወረዳው መላክ አለበት። በስርጭት ጣቢያ የተራገፈው መጠን ከማዕከላዊ መጋዘን ከተላከው ጋር ለማመሳከር ይጠቅማል። ሪፖርቱ የሚያካትተው ባለፈው ወር ወደ ስርጭት ጣቢያው የገባውን የዕርዳታ መጠን፣ ከአ/መ/ዝ/መ/ዋ/ዘ ማዕከላዊ መጋዘን ዕርዳታው ሲላክ ወጪ የተደረገበት ሠነድ ቁጥር እና በስርጭት ጣቢያው ሲራገፍ ገቢ የተደረገበት ሠነድ ናቸው። በተጨማሪም ከስርጭት ጣቢያ የተከፋፈሉ እና ገቢ የተደረጉ እንዲሁም በጉዞ ወቅት የጠፋትን/የተበላሹትን ይጨምራል።

- **የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የክምችት ሁኔታ ሪፖርት** (በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰራበት ግልባጭ ያለው ፓድ/ጥራዝ) ፡- ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን ወርሃዊ ሪፖርቱን አጠናቃችሁ ወደ ወረዳው

መላክ አለባችሁ፡፡ አጠቃላይ ገቢ የተደረገ የዕርዳታ መጠን፣ በቀደመው ወር ከስርጭት ጣቢያ የተከፋፈለና የወሩ መጀመሪያ ከወጪ ቀሪ፣ በመጋዘን የተበላሸ እና የወሩ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ በአጠቃላይ በስርጭት ጣቢያ መጋዘን ገቢና ወጪ የተደረጉትን የሚያሳይ ነው፡፡

በክልላዊ መንግስት የሚሰጡ ግልባጭ ያላቸው ሰነዶች(የመረከቢያና የስርጭት ጣቢያ የወጪ ሠነዶች) ስማቸው በየክልሉ ሊለያይ ይችላል፡፡



ከላይ የተጠቀሱትን ማንኛውንም ግልባጭ ያላቸውን ጥራዞች፣ ካርዶችና ሌጀር/መዝገብ ካላገኛችሁ ለቅርብ አለቃችሁ በአስቸኳይ ማሳወቅ ይኖርባችኋል፡፡

ደረጃ 2: የዕርዳታ ቁሳቁሶቹ የሚራገፉበትን ቀን ለወዛደሮች ታሳውቃላችሁ

ዕርዳታውን ለሚያራገፉ ወዛደሮች እንደሚገኙ ለማረጋገጥ የመረከቢያውን ቀን ግምት ታሳውቋቸዋላችሁ፡፡



ደረጃ 3: የስርጭት ጣቢያ መጋዘኑን ታጸዳላችሁ


መደበኛ በሆኑት የቀን ፣ ሳምንታዊና ወርሃዊ የጊዜ ሠሌዳዎች መሰረት የስርጭት ጣቢያ መጋዘኑ ዕርዳታው ከመራገፉ አስቀድማችሁ መጽዳቱን ታረጋግጣላችሁ፡፡ የሚከተሉት ለዝግጅት የሚያስፈልጉ ነገሮች ናቸው፡፡

የመጋዘኑን የውስጥ ክፍል ማጽዳት፣	የመጋዘኑን ውጫዊ ክፍል ማጽዳት፣
	
ሁልጊዜ ጥራጊውን ከመጋዘኑ ራቅ አድርጎ መድፋት፣	ለአይጦች መደበቂያ ስለሚሆን አረሞችንና ቆሻሻዎችን ማስወገድ፣

የሚከተሉትን የጽዳት ቀናት ማክበር አስፈላጊ ነው፡-

- በየቀኑ የመጋዘኑን ወለል ማጽዳት ፣
- በየሳምንቱ ግድግዳውንና የድርድሩን ጎኖች ማጽዳት ፣
- በወር አንዴ መጋዘኑን በጠቅላላ ማጽዳት ፤ በተለይ መጋዘኑ ባዶ ከሆነ ሙልጭ አድርጎ ማጽዳት ናቸው ፡፡

ጠቅላላ መጋዘኑን የማጽዳት ቅደም ተከተል እንደሚከተለው መሆን አለበት፡- መጀመሪያ መጋዘኑን ከላይ ወደ ታችኛው ክፍል ማጽዳት ፤ በመቀጠል ከበሩ ርቀው ያሉትን አካባቢ ጀምሮ ወደ በሩ ማጽዳት ፡፡	
የመጋዘኑ የላይኛው ክፍል በሚጸዳበት ወቅት የቤቱ ክዳን ያረፈበትን ማገር/ ግንብና የግድግዳዎቹን የላይኛውን ክፍል ማጽዳት፡፡ ጥራጊዎች ድርድሩ ላይ እንዳይራገፉ የፕላስቲክ መሸፈኛ መጠቀም ፡፡	

ግድግዳው በንጽህና መያዝ አለበት ፣ ግድግዳውና ወለሉ የሚገናኙበትንና ጥጋጥጉን በሚገባ ማጽዳት ፣	
ወለሉንና የድርድሩን ጎኖች ጽዳት መጠበቅ ፣	የመጋዘን በሮችንና መቀርቀሪያዎቹን ማጽዳት ፣
	

ደረጃ 4: የድርድሩን ስፋትና ከፍታን ትወስናላችሁ መደርደሪያዎች ካሉም ታስተካክላላችሁ

የዕርዳታ ቁሳቁሱን ከመረከባችሁ በፊት በአካባቢው የሚገኝ ከሆነ መደርደሪያውን በትክክለኛ ስፍራ በማድረግ ስለ ድርደራው ማቀድና መዘጋጀት አስፈላጊ ነው ፡፡

አስቀድሞ ለእያንዳንዱ የዕርዳታ ቁሳቁስ የሚያስፈልገውን የቦታ ስፋት ማስላት ይጠበቅባችኋል ፡፡ (የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የመጋዘኑን አቅም ስለማስላት የተጸፈውን ማብራሪያ በክፍል 7 ተመልከቱ (የስርጭት ጣቢያ መጋዘንን የመያዝ አቅም ማስላት ማብራሪያን ተመልከቱ) ፡፡

- የሚራገፈው የዕርዳታ መጠን ፣
- የቁሳቁሱ ዓይነትና እሽጋቸው/ጥቅሉ ፣
- እሽጉ/ጥቅሉ የሚፈጀው ቦታ ፣
- የድርድሩ ከፍታ በሚከተሉት ነገሮች ሊወሰን ይችላል ፤
  - የእሽጉ አይነት ፣


- የስርጭት ጣቢያ መጋዘኑ ከፍታ፣

- የድርድሩ ወርድ/የጎን ስፋት - የድርድሩ ቁመት ከጎን ስፋቱ መብለጥ የለበትም፡፡

ከላይ በተዘረዘሩት መሰረት የአደራደሩን ዕቅድ ማዘጋጀት ይኖርባችኋል፡፡



ሠራተኞቹ በድርድሩ መሀል እንደልብ ተንቀሳቅሰው መስራት እንዲችሉ በቂ ቦታ መኖር አለበት - (ከ60 ሳሜ - 1 ሜ)፡፡




ሠራተኞቹ በእያንዳንዱ ድርድር በመመላለስ መስራት እንዲችሉ የመረማመጃው ስፋት ከሚያስፈልገው ስፋት ያነሰ መሆን የለበትም (ከ1 ሜ - 1.5 ሜ)ቁሳቁሶቹ በሚራገፉበት ወቅት በቀላሉ ለመደርደርና ድርድሩን ለመከፋፈል የመረማመጃ ቦታ አመቺ መሆን አለበት፡፡



ድርድሮቹ በሚያርፉበት ወቅት በቂ የእግር መመላላሻ ቦታ እንዲኖር በወለሉ ላይ የሚቀባው መስመር እንደ ምልክት ያገለግላል፡፡

የሴፍቲኔት እና የዕለት ዕርዳታ ቁሳቁሶች ለየብቻ መደርደር አለባቸው፡፡ ሌላ ተጨማሪ ፕሮግራም የሚካሄድ ከሆነ ድርድሩ ለብቻ መሆን አለበት፡፡

ለተለያዩ የምደባ ዙር/ወር የሚመደቡ ዕርዳታዎች ለየብቻ መደርደር አለባቸው፡፡




ከአጠቃላይ የመጋዘን ከምችት የምግብ ቁሳቁሶች ለብቻ ተለይተው መቀመጥ አለባቸው።።

ከምግብ ጋር ለእርሻ የሚያገለግሉ ኬሚካሎችን ለምሳሌ ፀረ-ተባይና ማዳበሪያ ወይም ሲሚንቶ በአንድ መጋዘን በፍጹም መቀመጥ የለባቸውም።።


ከእርጥበት ለመከላከልና በቂ አየር እንዲዘዋወር ድርድሮች ከመሬት ከፍ ባለ ርብራብ (dunnage) ላይ መቀመጥ አለባቸው።። ጠንካራ የዕቃ መደርደሪያ ድርድሩን ጠንካራ ያደርገዋል።። ጥቂት የዕቃ መደርደሪያዎች ብቻ የሚገኙ ከሆነ ለዱቄትና ለቅይጥ/አልሚ ምግቦች ቅድሚያ መሰጠት አለበት።።

የመደርደሪያ ዕቃዎች አይነት


ከጣውላ የሚሰራ ርብራብ



ከአጣና የሚሰራ ነጠላ ርብራብ




ከአጣና የሚሰራ ድርብ ርብራብ




የመደርደሪያ አጠቃቀም

ርብራቦቹ ውሃልካቸው የተጠበቀ መሆን አለበት ያለበለዚያ ድርድሩ ሊፈርስ/ሊናድ ይችላል




ርብራቡ ላይ የሾለ ወይም የተሰነጠረ ወይም ያልተሞረደ ስል ነገር ካለ መወገድ አለበት ፤ ካልሆነ ግን ከሰር ያለውን ጆንያ በመቅደድ እህሉ እንዲፈስ ሊያደርግ ይችላል።።





በስዕሉ በሚታየው መሰረት ርብራቡ ተስተካክሎ መቀመጥ አለበት




3



የሰርዳታ ቁሳቁስ መረከብ

3 የዕርዳታ ቁሳቁስ መረከብ

ምስል 4፡ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የዕርዳታ ቁሳቁሶችን መረከብ-የስራ ሂደቶች



ደረጃ 1: ከአሽከርካሪው ጋር ትገናኛላችሁ

ከማዕከላዊ መጋዘን ከተላከ በኋላ ዕርዳታውን የጫነ መኪና ስርጭት ጣቢያ ይደርሳል፡፡ በመደበኛው የስራ ሰዓታችሁ በቦታው በመገኘት ዕርዳታውን እንደምትረከቡ ማረጋገጥ አለባችሁ፡፡

የመኪናው አሽከርካሪ የስርጭት ጣቢያው የሚገኝበትን አካባቢ መለየት ካልቻለ በክልሉ የሚመለከተውን ቢሮ ሥልክ ደውሎ መጠየቅ ይኖርበታል፡፡ የክልል ቢሮውም የመጋዘን ሰራተኞችን ወይም የቅርብ አለቃቸውን ስልክ ቁጥር በቀጥታ ደውሎ እንዲያገኛቸው ለአሽከርካሪው ይሰጣል፡፡

ከአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የተላከውን የወጪ ሠነድ በመጀመሪያ በመመልከት የመዳረሻ ስርጭት ጣቢያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ይኖርባችኋል፡፡ ስርጭት ጣቢያዉ ትክክለኛው ካልሆነ ዕርዳታውን መረከብ የለባችሁም፡፡ ነገር ግን መኪናውን ትክክለኛ ወደሆነ ስርጭት ጣቢያ መምራት ይኖርባችኋል፡፡ ትክክለኛው የስርጭት ጣቢያ የት እንደሆነ የማታውቁ ከሆነ የቅርብ አለቃችሁን ማነጋገር ይኖርባችኋል፡፡

የደረሰው ዕርዳታ በወጪ ሠነዱ ላይ ከተመለከተው ፕሮግራም ፣ የዕርዳታ ዙር እና የድልድል መጠን ጋር ተመሳሳይ መሆኑን (የተጠየቀው ብዛት ከአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የወጪ ሰነድ ጋር መመሳሰሉን) ማረጋገጥ አለባችሁ፡፡ ከነዚህ መስፈርቶች ውስጥ አንዳች የተለየ ነገር ካጋጠማችሁ ከቅርብ አለቃችሁ መመሪያ መጠየቅ አለባችሁ፡፡

> ተሸከርካሪው **በወሩ የመጀመሪያ ቀን** ለማራገፍ በስርጭት ጣቢያ ቢደርስ ከመራገፉ በፊት ወርሃዊ ቆጠራውን እና ሪፖርቱን እስከምታጠናቅቁ ድረስ አሽከርካሪው መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ *ክፍል 5 ወርሃዊ ሪፖርት አዘገጃጀትን* ተመልከቱ፡፡

ደረጃ 2: ከጭነት መኪናው ከመራገፉ በፊት የዕርዳታ ቁሳቁሱን ትፈትሻላችሁ

የስርጭት ጣቢያው በወጪ ሠነዱ ላይ እንደተመለከተው ትክክለኛ ሆኖ ከተገኘ ዕርዳታውን ከመኪናው ላይ ከማውረዳችሁ በፊት መፈተሽ አለባችሁ፡፡ በዚህ ወቅት ማንኛውም እርጥበት ፣ ብልሽት ወይም የተባይ ወረርሽኝ ምልክቶች ከታዩ ከመረከባችሁ በፊት ለቅርብ አለቃችሁ ሪፖርት ማድረግ አለባችሁ፡፡


የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን የዕርዳታ ቁሳቁሶችን የምትረከቡበት የተለየ ትዕዛዝ ወይም ዕቃዎቹ ጥቅም ላይ መዋል የሚችሉ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ከደረሳችሁ ብቻ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ወዲያዉኑ ለቅርብ አለቃችሁ በማሳወቅ መመሪያዎችን መጠበቅ አለባችሁ፡፡

ማሳሰቢያ፥ ችግር ስለመኖሩ ለቅርብ አለቃችሁ ካሳወቃችሁ በ24 ሠአት ውስጥ የሚመለከተውን የክልሉ ቢሮ በማግኘት መመሪያ መጠየቅ ይኖርበታል ፡፡

ጭነቱን ከተበላሹ ዕቃዎች ጋር ከተረከባችሁ የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅባችኋል፡-

1. **የብልሽቱን አይነትና መጠን በመግለጽ ዕቃዎቹ የተበላሹ ስለመሆናቸው ትፈርማላችሁ** *(ከታች ደረጃ 5፣ የመረከቢያ ሠነድ ታዘጋጁና ኦርጂናል ቅጅውን ለአሽከርካሪው ትሰጣላችሁ የሚለዉን ተመልከቱ)*
2. **በከምችት ወቅት ለተበላሹ ዕቃዎች የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባችኋል** *(ደረጃ 3፣ ቁሳቁሶችን ማውረድ፣ መቁጠርና መደርደር የሚለውን ተመልከቱ)*፡፡

ደረጃ 3: የዕርዳታ ቁሳቁሶችን ማዉረድ፣ መቁጠርና መደርደር



ወዛደሮቹ የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸማቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባችሁ፡-

1. ብክነትን ለመቀነስ ሲባል ቁሳቁሶቹን ሲያወርዱና ሲደረድሩ በተገቢው ጥንቃቄ እና መልካም በሆነ የቁሳቁስ አያያዝ ሥርዓት ተግባራቸውን መፈጸማቸውን፣


2. ቁሳቁሶቹን ሲደረድሩ በተቀመጠው ፕላን መሰረት መስራትና የተበላሹ ካሉ ለይተው ማስቀመጣቸውን፣

በዚህ ሂደት ውስጥ የተረከባችሁትን የዕርዳታ ቁሳቁስ በመረከቢያ ሠነድ ላይ ለመመዝገብ እንዲያመቻችሁ ዕቃዎቹን መቁጠር አስፈላጊ ነው፡፡

ወዛደሮቹ የዕርዳታ ቁሳቁሶቹን በተገቢው ጥንቃቄ መያዛቸውን ማረጋገጥ የእናንተ ኃላፊነት ነው።። የዕርዳታ ቁሳቁሶቹ በስርጭት ጣቢያው ከደረሱ በኋላ ጉዳት ቢደርስና እንደገና ማሸግ ቢያስፈልግ ከክልል በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ከሚቴ በማቋቋም በድጋሚ ማሸግ ይቻላል ይህም ብክነትን ለመቀነስ ያስችላል።።

እያንዳንዱን የዕርዳታ ቁሳቁስ የያዘ ዕቃ በመፈተሽ ቀጥሎ በተመለከተው መሰረት መለየት ያስፈልጋል።።


1. የተጎዱ ከረጢቶች ምሳሌ፥



የተበሳ ከረጢት




የተተረተረ ከረጢት




የተጨማደደ እሽግ

2. የረጠበ/ ውሀ የያዙ ከረጢቶች



የረጠበ ከረጢት

3. የተከፈተ እሽግ




የተከፈተ ካርቶን




ያልተሰፋ ከረጢት

4. የሚያፈስና የሚያንጠባጥብ




የብረት በርሜል



የፕላስቲክ መያዣዎች

5. የውስጥ ከፍላቸው የተጎዱ ካርቶኖች




የተጨማደደ ጣሳ




ያበጠ ጣሳ

6. በእሸጉ ዙሪያ ተባዮች ሲሰፍሩ





7. ተባዮች በምግብ ቁሳቁስ ላይ ሲሰፍሩ ወይም የነቀዘ ምግብ



ይህ የሚታወቀው የምግቡን ናሙና ተወስዶ ከተመረመረ ነው

8. ክብደታቸው የቀነሰ ከረጢቶች (ዕቃውን በማንሳት ፣ በማየት ወይም ሚዛን የሚገኝ ከሆነ በመመዘን) ፣






ከላይ ከተዘረዘሩት ጉድለቶች/ ችግሮች ሲያጋጥማችሁ የሚከተሉትን ማድረግ ያኖርባችኋል፥-


- የተበላሹትን ዕቃዎች ከሌሎች ዕቃዎች መለየት ፣
- የተበላሹ ዕቃዎችን ብዛት መመዝገብ ፣
- የተበላሹ ጥቅሎችን ለብቻ መደርደር (በአይነት የተበላሹትን ለብቻ መደርደር)
- የረጠቡ ጥቅሎችን በመመሪያው መሰረት ማስተናገድ ፣፣

በመቀጠል በተቻለ ፍጥነት (እንደ አስፈላጊነቱ ተቆጣጣሪ ኮሚቴ በተገኘበት) የሚከተሉትን ማከናወን፥-

1. የተበላሹ ጥቅሎችን መጠገን ፣



ከረጢቱን በመስፋት




በፖላስተር በማሸግ

2. የተከፈቱ መያዣዎችን እንደገና በማሸግ ፣




በአዲስ ከረጢት እንደገና ማሸግ ፣




በሌላ ከረጢት ውስጥ ማስቀመጥ ፣

3. የተጠገኑ እሽጎችን ለብቻ መደርደር ፣





ከዋናው ድርድር ጎን ለጎን መደርደር



ወይም ከነባሮቹ/ከደህናዎቹ ድርድር በላይ መደርደር

የሚያፈስ የዕህል ከረጢት እንደገና በከረጢት በማሸግ የሚቻል ከሆነ ከቀድሞ ክብደት ልክ እንዲሆን ማድረግ ፣ የሚያንጠባጥቡ የዘይት መያዥያዎችን እንደገና በአዲስ መያዣ መገልበጥ (የሚገኝ ከሆነ) ፡፡

ማሳሰቢያ ፦ በተበላሸ መያዣ የተቀመጠ ምግብ ለአገልግሎት ብቁ ላይሆን ይችላል ፡፡

ጥንቃቄ የተሞላ አያያዝ ምግቦች እንዳይበላሹና ብክነትን ለመቀነስ ይረዳል ፡፡


ከረጢቶችን መሸከም እንጂ መንተት ተገቢ አይደለም - የሚገኝ ከሆነ ጋሪ ተጠቀሙ








መንጠቆ አለመጠቀም







እህሉ ከከረጢቱ ይፈሳል

አለመወርወር ወይም አለመጣል - ይህ ድርጊት ከረጢቶቹ እንዲቀደዱ ያደርጋል በተለይ የወረቀት ከረጢቶች ከሆኑ







በዝናብ ውስጥ አለማራገፍ	እርጥበት የወረቀት ከረጢቶችንና ካርቶኖችን ጥንካሬያቸውን ይቀንሳል	ዱቄት ወይም ጥራጥሬ እርጥበት ከነካው ይሻግታል ፤ ጥራጥሬው እንደገና ሊበቅል ይችላል
		


ማሳሰቢያ


- የተበላሹና የተጠገኑ ከረጢቶቸን ለብቻ መደርደር አለባቸው ፣
- ድርድሮች በተቀመጠው ፕላን መሰረት መደርደራቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ፣
- በቀላሉ ለመቁጠር እንዲያመች በስርዓት መደርደር ፡፡ ለምሳሌ ሁለት አይነት የከረጢት አደራደር ስርዓቶች ሲኖሩ ርዝመቱ የወርዱን ሁለት እጥፍ የሆነ አደራደር ከዚህ በታች ተመልከቱ ፡፡

አደራደር


3 ጊዜ 10 ከረጢቶች = በእያንዳንዱ መስመር 30 ከረጢቶች	በእያንዳንዱ ክፍል 3 ከረጢቶች ይገኛሉ = በ2 አግድም መስመር አምስት ክፍሎች አሉት = በአንድ መስመር ላይ 30 ከረጢቶች ይገኛሉ
	


ድርድር መሰራት ያለበት እስከ መደርደሪያው ጥግ ድረስ መሆን አለበት





ድርድሩ እንዳይናድ በጥብቅ እርስበርስ በማስተሳሰር መደርደር አለበት







የጠበቀ ድርድር

ያልተሳሰረ/ ያልጠበቀ ድርድር



እያንዳንዱ ከረጢት ከሰሩ ከሚገኘው በተቃራኒ ከተደረደረ የጠበቀ/የተሳሰረ ድርድር ሊገነባ ይችላል ፡፡ ለምሳሌው ከሰር ይመልከቱ ፡፡







የመጀመሪያ ዙር ድርድር

ሁለተኛ ዙር ድርድር



	
ሶስተኛ ዙር ድርድር	አራተኛ ዙር ድርድር

እስከ ላይኛው የመጨረሻ ድርድር ድረስ ከላይ በተጠቀሰው መልክ መገንባት ፡፡ ሙሉ በሙሉ የድርደራውን ዙር እስከመጨረሻው የሚያሟላ ቢሆንም በተለምዶ የመጀመሪያዉ ዙሮች እንደተደረደሩ ከአንደኛው አቅጣጫ ድርደራው ስርአቱን ጠብቆ ሊገነባ ይችላል ፡፡ ቢሆንም የአደራደሩን ትክክለኛነት መጠበቅ አስፈላጊ ነው ፡፡

እንደ አማራጭ 3 ከረጢቶችን በመደዳ መደርደር የተሻለ የጠበቀ ድርድር መገንባት ይቻላል ፡፡

የድርድር ዙሮች አስተሳሰር 1,3,5,7...	የድርድር ዙሮች አስተሳሰር 2,4,6,8...
	

የከረጢቱ ርዝመት ከጎኑ 1.5 ጊዜ ሲተልቅ ድርድሩ በመደዳ 5 ከረጢቶችን በማስቀመጥ ሊገነባ ይችላል ፡፡



የድርድር ዙሮች አስተሳሰር 1,3,5,7...	የድርድር ዙሮች አስተሳሰር 2,4,6,8...
	

ከረጢቶቹ ከድርድሩ ቀስ በቀስ የሚቀነሱ ከሆነ በመደዳ 3 ወይም 5 ከረጢቶችን መደርደር ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ የድርድር መስመር ሲነሳ የድርድሩ ጎን ቀጥ ብሎ እንዲቆይ ይረዳል፡፡


ስለ እሸጎች የተሰጠውን የአደራደር መመሪያ ተመልከት፡፡ በቆርቆሮ ወይም በጠርሙስ የሚገኝ የምግብ ዘይት አናቱ ቀና ብሎ መደርደር አለበት አለበለዚያ ሊያንጠባጥብ ይችላል፡፡

> *የእርዳታ ቁሳቁሶቹን በምታራግፉበትና በምትደርድሩበት ወቅት ብዛታቸው እኩል የሆኑ ከረጢቶች በእያንዳንዱ የድርድር መስመር መደርደራቸውን ስታረጋግጡ በየወሩ መጀመሪያ ቀን የምታካሂዱትን ቆጠራ በቀላሉ ማከናወን እንድትችሉ ይረዳችኋል፡፡*
> *ማሳሰቢያ፡- የቁሳቁስ አደራደር ስርዓት ላይ ወዛደሮቹን ማሰልጠን አስፈላጊ ነዉ*


ድርድሩን እስከተወሰነ ከፍታ መገንባት ነገር ግን ምርመራ ለማካሄድና ተባዮችን ለማጥፋት እንዲቻል በድርድሩ ከፍታና በጣሪያው መካከል በቂ ከፍተት ሊኖር ይገባል፡፡


በድርድሩና በጣሪያው መካከል ከፍተት መስጠት	አየር እንዳይዘዋወርና በቀላሉ እንዳይደረስ ስለሚያደርግ ድርድሩ እስከ ጣሪያው ጥግ ድረስ መሆን የለበትም፡፡
	

የተገነባው ድርድር ሊናድ ስለሚችል የድርድሩ ከፍታ እስከ ጣሪያው ጥግ መድረስ ወይም የቤቱ ክዳን መደገፊያ የሆነው ማገር ላይ መደርደር የለበትም ፡፡



የድርድሩ ግንባታ አስተማማኝ ላይሆን ስለሚችል እና ከታችኛው ክፍል የሚገኙትን ሊጎዳና እንዲፈስ ሊያደርግ ስለሚችል ከፍታው አላስፈላጊ ደረጃ ድረስ መሆን የለበትም ፡፡





- የሴፍቲኔት እና የዕለት ዕርዳታ ቁሳቁሶች ለየብቻ መደርደር አለባቸው በተጨማሪም የሌላ ፕሮግራም ቁሳቁሶችም ድርድራቸው ለብቻ መሆን አለበት ፡፡

- ለተለያዩ የምደባ ዙር/ወር የሚመደቡ ዕርዳታዎች ለየብቻ መደርደር አለባቸው ፡፡

ደረጃ 4: የስርጭት ጣቢያ ሌጀር/መዝገብ በየጊዜው ማስተካከል



የስርጭት ጣቢያ ሌጀር/መዝገብ በስርጭት ጣቢያ *መጋዘን* የሚገኘውን የክምችት ሁኔታ የሚገልጽ ሲሆን ምንጊዜም ዕቃ ከመጋዘኑ ወጪ ወይም ገቢ እንደተደረገ መስተካከል አለበት።።

ቆጠራው እንደተጠናቀቀ የስርጭት ጣቢያው ሌጀር/መዝገብ ወዲያው መስተካከሉን ማረጋገጥ አለባችሁ።።

አስፈላጊነቱ ከዚህ በታች ተዘርዝሯል፦

- የዕርዳታዎችን የክምችት ሁኔታ በትክክል መዝግቦ ለማቆየት፣
- የተረከባችሁትን የተለያዩ የዕርዳታ አይነቶች ለቅርብ አለቃ ለማሳወቅ፣
- የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የክምችት ሁኔታ ሪፖርቶችን ለማጠናቀር፣

ማሳሰቢያ ፦ የስርጭት ጣቢያው ቋሚ ከሆነ የስርጭት ጣቢያ ሌጀር/መዝገብ በዚያው ሊቀመጥ ይችላል ቋሚ ካልሆነ ግን በወረዳው ጽ/ቤት መቀመጥ አለበት።።

ቢን/ስቶክ ካርድ የምትጠቀሙ ከሆነ የዕርዳታ ቁሳቁስ በሚደረደርበት ወቅት በማዘጋጀት በቀላሉ ሊታይና ሊደረስበት የሚችልበት የድርድሩ ጎን ላይ መለጠፍ አለባችሁ።። ለዚህ ዓላማ የተዘጋጁ ካርዶች የማይገኙ ከሆነ እና በተለያዩ ፕሮግራሞች የመጡ ቁሳቁሶች ካሉ እና/ወይም በተለያዩ የምደባ ዙሮች/ወራት ወደ ስርጭት ጣቢያ በአንድ ላይ ተከማችተው የሚገኙ የዕርዳታ ቁሳቁሶችን ለመለየት ከወረቀት የተዘጋጀ ካርድ በድርድሮቹ ጎን መለጠፍ ይኖርባችኋል።። ይህ የእያንዳንዱን ፕሮግራም የቁሳቁስ እንቅስቃሴና የምደባ ዙር/ወር ለያይቶ ሪፖርት ለማድረግ ይረዳል።።

ማሳሰቢያ ፦ በመጋዘን ከተደረደው የዕርዳታ ቁሳቁስ ላይ ወጪ ወይም ገቢ ከተደረገ በኋላ የሚቀረውን የክምችት መጠን ለማሳየት የሚረዳ ቢን/ስታክ ካርድ ነው።። የሚይዙት መረጃ ብዛትን ነው ማለትም የከረጢት ወይም የካርቶን ብዛት እንጂ ከብደታቸውን አይደለም።። ከዚህም በተጨማሪ ቢን/ስቶክ ካርድ ስለ ፕሮግራም ዝርዝር ሁኔታ፣ የምደባ ዙር/ወር፣ ስለተደረጉ ምርመራዎች፣ አዲትና ፀረ-ተባይ የተረጨበትንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ለመያዝ ይጠቅማል።። በድርድሩ በጎን በኩል በሚታዩበት ሁኔታ በቋሚ ሰፍራ ይሰቀላል።።

አሽከርካሪው ለወላጆቹ ክፍያ ይፈጽማል

ለወላጆቹ ክፍያ መፈጸም የአሽከርካሪው ሐላፊነት ነው። ለዚህም የሚሆን ጥሬ ገንዘብ በፈጌራል ደረጃ በተደረሰው የክፍያ መጠን መሰረት ይዞ መገኘት አለበት። ወላጆቹም ክፍያውን ለመቀበላቸው ማረጋገጫ እንዲሆን ደረሰኝ መስጠት አለባቸው።

ደረጃ 5: የመረከቢያ ሠነድ ማዘጋጀትና ኦርጅናል ሰነዱን ለአሽከርካሪው መስጠት

የመረከቢያ ሰነዱን ስታዘጋጁ ከአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የተላከውን የወጪ ሠነድ በመመልከት በሰነዱ ላይ የሚከተሉትን መጥቀስ ይኖርባችኋል፦

1. የአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የወጪ ሠነድ ቁጥር ፣
2. የተረከባችሁትን የዕርዳታ መጠን (ዕቃው ሲራገፍ በተደረገው ቆጠራ መሰረት) ፣
3. የጠፋው የዕርዳታ ቁሳቁስ ብዛትና የጠፋበት ምክንያት (ከአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ ማዕከላዊ መጋዘን የተላከው ቁሳቁስ ከተራገፈው በላይ ከሆነ) ፣
4. ዕርዳታዎቹ እንደደረሱ መበላሸታቸው ከተረጋገጠ (እንደተራገፉ ለብቻ መደርደር)።

የዕርዳታ ቁሳቁስ የጠፋበትን ምክንያት መለያ ኮድ ዝርዝር ብቻ መጠቀም እና የጠፋበትን ምክንያት በተሻለ የሚገልጸውን ከተሰጡት መለያ ኮዶች በመምረጥ መፃፍ።

እናንተና አሽከርካሪው በመረከቢያ ሰነድ ላይ መፈረም ይኖርባችኋል።

የአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የወጪ ሰነድ ቁጥርን በመረከቢያው ሰነድ ላይ መመዝገባችሁ በጣም አስፈላጊ ነው።





በመረከቢያ ሠነድ ላይ በተቀመጠው መመሪያ ሳይሆን በበካርድ ቁ. 3 የተጠቀሰውን መመሪያ በመከተል የመረከቢያ ሰነድ ቅጅዎችን ማሰራጨት ይኖርባችኋል፡፡ ማሳሰቢያ፡- በአንዳንድ ክልሎች ኦርጅናል ቅጂና ተጨማሪ ኮፒ መስጠት ሊኖርባችሁ ይችላል፡፡



መረከቢያ ሰነዱ ላይ ማህተም ለማስመታት አሽከርካሪው ወደ ወረዳ ጽ/ቤት ይሄዳል፡፡

ኦሪጅናል የመረከቢያ ሠነድ ላይ ማህተም እንዲያደርግለት አሽከርካሪው ወደ ወረዳ ጽ/ቤት ይሄዳል፡፡ የማመላለሻ (የአጓጓዥ) ድርጅቱ ከፍያ እንዲፈጸምለት የአ/መ/ዘ/ም/ዋ/ዘ አሰራር ይህን ያዝዛል፡፡

ደረጃ 6: የአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ ወጪ ሰነድ ጋር በማያያዝ ቀሪ የመረከቢያ ሰነድ ግልባጮችን ማሰራጨት

በክልሉ መመሪያ መሰረት የመረከቢያ ሠነድ ቀሪ ግልባጮችን (ለአሽከርካሪው የሚደርሰውን ከሰጣችሁ በኋላ) ለሚመለከታቸው ታሰራጫላችሁ፡፡



በመረከቢያ ሠነድ ላይ በተቀመጠው መመሪያ ሳይሆን በካርድ ቁ. 3 የተጠቀሰውን መመሪያ በመከተል የመረከቢያ ሰነድ ቅጅዎችን ማሰራጨት ይኖርባችኋል፡፡



ከአሽከርካሪው የተረከባችሁትን የአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የወጪ ሠነድ በፖዱ ላይ ከሚቀረው የመረከቢያ ሰነድ ጋር ታያይዙታላችሁ/ትሰፋታላችሁ፡፡ ይህ የመንግስት የኦዲት መመሪያ ነው፡፡ የመረከቢያ ሰነድ ፖድ/ጥራዝ አለመግባባት በሚፈጠርበት ወቅት ወይም በኦዲት ጊዜ ከአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ ማዕከላዊ መጋዘን የተላኩትን እና በሰርጭት ጣቢያ መጋዘን የተራገፉትን ለማረጋገጥ እና ልዩነቶች ካሉ ለመመርመር ያገለግላል፡፡

ደረጃ 7: የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የገቢ ሪፖርት ማሻሻል



የተረከባችሁትን የዕርዳታ ቁሳቁሶች ለመግለጽ በየጊዜው የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የገቢ ሪፖርቱን ታሻሽላላችሁ፡፡ ይህም የሚከተሉትን ይዘረዝራል ፡-

1. የአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የወጪ ሠነድ ቁጥር ፣
2. የመረከቢያ ሠነድ ቁጥር ፣
3. ከመዕከላዊ መጋዘን የተላከውና ስርጭት ጣቢያ ገቢ የተደረገዉ የዕርዳታ መጠን ፣
4. ስለጠፉ ዕቃዎች የተሰጡ ምክንያቶች፡፡

ለእያንዳንዱ ፕሮግራም የተለያዩ ግልባጭ ያላቸው ፓዶችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም አዲስ ሪፖርት ሲጀመር በኢትዮጵያ የወር አቆጣጠር በእያንዳንዱ ወር የመጀመሪያው ቀን ላይ መሆን አለበት (የጳጉሜ ሪፖርት ከነሐሴ ጋር በአንድነት ይቀርባል)፡፡

የሴፍቲኔት እና የዕለት ዕርዳታ ፕሮግራም ቁሳቁሶች በተመሳሳይ የሪፖርት ወር ውስጥ በአንድ የስርጭት ጣቢያ ገቢ ቢሆኑ ለእያንዳንዱ ፕሮግራም የየራሱ ሪፖርት መዘጋጀት አለበት፡፡ (በአጠቃላይ ሁለት ሪፖርት ይዘጋጃል)፡፡

በመንግስት ወርሃዊ ሪፖርት መመሪያ መሰረት ወር በገባ በ30ኛው ቀን ሪፖርቱ ተጠናቅቆ ለወረዳው መላክ አለበት፡፡ ክፍል 5 ወርሃዊ ሪፖርት አቀራረብ ተመልከቱ፡፡

ወደ ስርጭት ጣቢያው ገቢ የተደረገውን ለማረጋገጥና ከማዕከላዊ መጋዘን የተላከውን ለማመሳከር ይህ ሪፖርት አስፈላጊ ነው፡፡ ወቅቱን የጠበቀና ትክክለኛ ሪፖርት አለመላክ ምርመራ በማካሄድ ተጠያቂውን ሊያስቀጣ ይችላል፡፡


4



የዕርዳታ ቁሳቁስ ማሰራጨት

4 የሰርዳታ ቁሳቁስ ማሰራጨት

ምስል 5፡ የሰርዳታ ቁሳቁስ ማሰራጨት - የስራ ሂደት ደረጃዎች



የስርጭት የጊዜ ሠሌዳ ማሳወቅ

በአስገዳጅ የጊዜ ሠሌዳ መሰረት በየስርጭት ጣቢያው የእያንዳንዱ ቀበሌ ተጠቃሚዎች መቼ መገኘት እንዳለባቸው የሚገልጽ የስርጭት/ክፍያ የጊዜ ሠሌዳ ወረዳው ያዘጋጃል፡፡ የስርጭቱ የጊዜ ሠሌዳ/ ቀናት ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ይገለጻል፡-

1. ለቀበሌ ሊቃነመናብርት፤ ሊቃነመናብርቱ ተረጂዎችን ከየቀበሌያቸው የማሰባሰብ ኃላፊነት አለባቸው ፣
2. ከስርጭት ጣቢያ መጋዘን የዕርዳታ ቁሳቁሶቹን ለማስረከብ እንደ መጋዘን ሰራተኝነታችሁ የምትገኙ መሆናችሁን ታረጋግጣላችሁ፣
3. ስርጭቱን ለመቆጣጠር ከወረዳው ለተወከለው ግለሰብ

ያልታሰበ ድንገተኛ አደጋ ካላጋጠመ በስተቀር በሰራችሁ በሚገኙ የስርጭት ጣቢያዎች ቆጠራ ለማካሄድና ወርሃዊ ሪፖርት ለማዘጋጀት እንዲረዳችሁ በኢትዮጵያ ቀን አቆጣጠር ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን ጠዋት ላይ ስርጭት ሊካሄድ አይችልም፡፡

ተረጂዎች በስርጭት ጣቢያው ይገኛሉ

የቀበሌው ሊ/መንበር በተጠቀሰው የስርጭት ቀንና ሰዓት ከተረጂዎች/ተጠቃሚዎች ጋር በመሆን በስርጭት ጣቢያው ይገኛል፡፡ በበቂ ምክንያት (ለምሳሌ፤ ህመም ፣ መኖሪያን በመቀየር ወዘተ) ካልቀሩ በስተቀር ሁሉም ተረጂዎች/ተጠቃሚዎች በስርጭት ጣቢያው መገኘታቸውን ማረጋገጥ የቀበሌው ሊ/መንበር ሐላፊነት ነው፡፡

አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የቀበሌው ሊ/መንበር የተሰጠውን ሐላፊነት ለሌላ የቀበሌ ግብረ ኃይል አባል በፅሁፍ ሊወክል ይችላል፡፡

በተለየ ምክንያት (ለምሳሌ፡- የስርጭት ጣቢያዉ ከተጠቃሚዎች በጣም የራቀ ከሆነ ተጠቃሚዎቹ የስርጭት ጣቢያዉ ድረስ እንዲሰበሰቡ ከመጠየቅ ለስርጭት ኮሚቴዉ ቁሳቁሶቹን ከስርጭት ጣቢያዉ ወስዶ ለተጠቃሚዎች በአቅራቢያቸዉ ሊያከፋፍላቸዉ ይችላሉ፡፡

የእርዳታ ቁሳቁሶቹን ለማሰራጨት ወረዳው መመሪያ ይሰጣል/ይፈቅዳል

በጸደቀው የዕቃ መጠየቂያና መልቀቂያ ሰነድ መሰረት የተወሰኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን አይነትና ብዛት ዝርዝር እንዲያከፋፍል ለተፈቀደለት አካል (ማለትም ለቀበሌ ሊ/መንበር ወይም ተወካይ) ለማስረከብ እንድትችሉ ከወረዳው የስራ መመሪያ ይሰጣችኋል።።

ደረጃ 1: የስርጭት ጣቢያ የወጪ ሠነድ በማዘጋጀት ቅጅዎችን ለሚመለከታቸው ማሰራጨት

የዕቃ መጠየቂያ እና/ወይም የመልቀቂያ ሰነድ እንደደረሳችሁ ከወረዳው በተሰጣችሁ መመሪያ መሰረት ለተፈቀደለት አካል የምታስተላልፏቸውን ቁሳቁሶች ዓይነትና ብዛት በመግለጽ የስርጭት ጣቢያውን የወጪ ሰነድ ማዘጋጀት አለባችሁ።።

በመረከቢያ ሠነድ ላይ በተቀመጠው መመሪያ ሳይሆን በካርድ ቁ. 3 የተጠቀሰውን መመሪያ በመከተል የመረከቢያ ሰነድ ቅጅዎችን ማሰራጨት ይኖርባችኋል።።

ደረጃ 2: የስርጭት ኮሚቴዎች በተገኙበት የዕርዳታውን ቁሳቁስ ለቀበሌ ሊ/መንበሩ ማስረከብ

የስርጭት ጣቢያ የወጪ ሰነድ አዘጋጅታችሁ ቅጅዎችን እንዳሰራጫችሁ የተጠቀሱትን ቁሳቁሶች ከመጋዘኑ ማስወጣት ትችላላችሁ።። በወጪ ትዕዛዝና በስርጭት ጣቢያ ወጪ ሠነዶች መረጃ/መመሪያ መሰረት ለእያንዳንዱ ቀበሌ ትክክለኛው ብዛት እንደተሰራጨ ለማረጋገጥ እርዳታው ከመጋዘን በሚወጣበት ወቅት መቆጠር አለበት።። የስርጭት ኮሚቴው ቀበሌውን ወክሎ ለተገኘው የቀበሌ ሊ/መንበር (የተፈቀደለት አከፋፋይ) የተላለፈውን እርዳታ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በስፍራው መገኘት አለበት።።

የዕርዳታ ቁሳቁሶችን ስለ መላክ

ድርድሩ በሚፈርስበት ጊዜ ከረጢቱ ወይም ካርቶኑ ሳይወረወር ወይም ሳይጣል በጥንቃቄ መነሳት አለበት።። ድርድሩን በተለመደው መሰረት ከአንደኛው ጫፍ በመጀመር ደረጃ በደረጃ ማንሳት ያስፈልጋል።። ከረጢቶቹ ከመጋዘን በሚወጡበት ወቅት ልክ በዕርዳታ ርክክብ ወቅት እንደተደረገው በጥንቃቄ መሆን አለበት።።

የቁሳቁስ መያዣዎች

የዕርዳታ ቁሳቁስ መያዣዎች አጠቃቀም እንደየክልሉ ይለያያል፡፡ ለተጠቃሚዎች የሚከፋፈሉ፣ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ፣ ገበያ ላይ የሚሸጡ ወይም የሚወገዱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የተጻፈውን የክልሉን መመሪያ በማገናዘብ ወይም የበለጠ መረጃ ለማግኘት የቅርብ አለቃችሁን መጠየቅ ይኖርባችኋል፡፡

ደረጃ 3: በስርጭት ጣቢያ የሚገኙትን የስርጭት ጣቢያ መዝገብ ማቀናነስ እና የወጪ ትዕዛዝና የዕቃ መጠየቂያ ሰነዶችን ፋይል ማድረግ

በመጋዘን የቀረው የዕርዳታ መጠን ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ የዕርዳታ ቁሳቁሶቹን ከስርጭት ጣቢያ እንዳስወጣችሁ በመጋዘን የቀረውን ክምችት በመቁጠር የስርጭት ጣቢያ መዝገቡን ወዲያዉኑ ማስተካከል አለባችሁ፡፡

ማሳሰቢያ፡- የስርጭት ጣቢያው ቋሚ ከሆነ የስርጭት ጣቢያ ሊጀር በዚያው ሊቀመጥ ይችላል ቋሚ ካልሆነ ግን በወረዳው ጽ/ቤት መቀመጥ አለበት፡፡

በተጨማሪም የወጪ ትዕዛዝና የዕቃ መጠየቂያ ኮፒዎችን (ከወረዳው እንደተቀበላችሁ) በፖዱ ላይ ከሚቀረው የስርጭት ጣቢያ ወጪ ሠነድ ጋር በማያያዝ ፋይል መደረግ አለበት፡፡ ይህ የመንግስት የኦዲት መመሪያ ነው፡፡ የስርጭት ጣቢያ የወጭ ሰነድ ጥራዝ አለመግባባት በሚፈጠርበት ወይም በኦዲት ወቅት ከስርጭት ጣቢያው በወረዳው ትዕዛዝ መሰረት ወጪ የተደረጉ የዕርዳታ ቁሳቁሶችን ለማረጋገጥ ያገለግላል፡፡

የሥርጭት ኮሚቴ የዕርዳታ ቁሳቁሶችን ለተጠቃሚዎች ያከፋፍላል

ለተፈቀደላቸው አከፋፋዮች የእርዳታ ቁሳቁሶቹን ሃላፊነት አስተላልፋችኋል፡፡ ከወረዳው በተሰጣቸው የተጠቃሚዎች የስም ዝርዝር መሰረት የሥርጭት ኮሚቴው ዕርዳታውን ለተረጂዎች/ተጠቃሚዎች ማከፋፈል ይጀምራል፡፡ ይህ የስም ዝርዝር በሴፍቲኔት የመክፈያ ሰነድ በመባል ሲታወቅ በዕለት እርዳታ ፕሮግራም ደግሞ የቀበሌ ተረጂዎች ስም ዝርዝር ይባላል፡፡ የሚቀጥሉት የዚህ ክፍል ክፍሎች የእርዳታ ቁሳቁሶች እንዴት እንደሚከፋፈሉ (ለመረጃነት) እንዲሁም በስርጭት ወቅት በማሰራጫ ጣቢያ ያልተገኙ ተጠቃሚዎች ሲያጋጥሙ የሚመለሱ የዕርዳታ ቁሳቁሶች ወደ ማሰራጫ ጣቢያ መጋዘን አመላለስ አሰራር ደረጃዎችን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

የእርዳታ ቁሳቁሶች ስርጭት አሰራር

በሴፍቲኔት ፕሮግራም ክፍያ ለመቀበል ተከፋዩ ግለሰብ የሴፍቲኔት ተጠቃሚነት ካርድ ማሳየት አለበት፡፡ በክፍያ ካርዱ ላይ ለዕርዳታው ብቁ የሆኑ ሰዎች ዝርዝርና የሚደርሳቸው የዕርዳታ መጠን ይገኝበታል፡፡

በዕለት ዕርዳታ ፕሮግራም ግን የቀበሌው ግብረ ኃይል የተረጂዎች/ተጠቃሚዎችን ማንነት እንዲያረጋግጥ ይጠይቃል፡፡

የተረጂው/ተጠቃሚው ማንነት እንደተረጋገጠ የስርጭት ኮሚቴው ለግለሰቡ ወይም ለቤተሰቡ ለዕርዳታው ብቁ እንደሆነ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

የስርጭት ኮሚቴው የተመደበላቸውን ዕርዳታ እንደተረከቡ ለማረጋገጥ ተጠቃሚው/ተረጂው በመክፈያ ሰነድ/በቀበሌ ስርጭት ዝርዝር ላይ እንዲፈርም ያደርጋል፡፡

የሴፍቲኔት ተጠቃሚ/ ተረጂው የሚገባውን የእርዳታ መጠን እንደተረከበ የወረዳው ተወካይ በተጠቃሚው ካርድ ላይ የሚከተለውን ማሻሻያ ያደርጋል፡-

1. የአካባቢ የልማት ስራ የሰራባቸውን ቀናት ወይም ቀጥታ ድጋፍ የተደረገለትን ቀናት ፣
2. ክፍያ፡- በአይነትና በመጠን ፣
3. ክፍያው የተካሄደበት ቀን ፣

ተጠቃሚው/ተረጂው ክፍያውን በወቅቱ ሳይቀበል ቢቀር ፤ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር (ለምሳሌ ከዕድሜ ወይም ከአካል ጉዳት ጋር በተያያዘ) ከሆነ የተወከለ ሰው ክፍያውን ሊቀበልለት ይችላል፡፡ ነገር ግን አስቀድሞ ከቀበሌ ግብረ ኃይል ይሁንታን ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

ከክፍያ ወይም ከስርጭቱ ጋር በተያያዘ ተረጂዎች/ተጠቃሚዎች ምንም አይነት ክፍያ እንዲከፍሉ መጠየቅ የለባቸውም፡፡ በመክፈያ ሰነድ/ በቀበሌ ስርጭት ዝርዝር በተመለከተው መረጃ መሰረት ሙሉ ክፍያ መከናወን አለበት፡፡

ማሳሰቢያ፡-ተጨማሪ አልሚ ምግብ ስርጭት የሚኖር ከሆነ (ለምሳሌ በቆሎና አኩሪ አተር ቅይጥ (CSB) ከፍተኛ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ላለባቸው ሰዎች ከመደበኛው በተጨማሪ እንዲያገኙ ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን በተለይ (ከአምስት አመት በታች ለሆኑ ሕጻናትና ለነፍሰጡር ወይም ለሚያጠቡ እናቶች) ነው፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛው ከመደበኛው የዕርዳታ ምግብ በተጨማሪ እነዚህን ሰዎች በመለየት ተጨማሪ አልሚ ምግብ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በከፍተኛ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት የተጎዱ ተረጂዎችን/ተጠቃሚዎችን ጥቅም ስለሚያሳሳ ያለተጨማሪ መስፈርት በምንም አይነት መልኩ ተጨማሪ አልሚ ምግብ ለሁሉም ተረጂዎች/ተጠቃሚዎች በጅምላ መከፋፈል የለበትም፡፡

ስርጭቱ እንደተጠናቀቀ የስርጭት ኮሚቴ ተወካይ የሴፍቲኔት እና የእለት ዕርዳታ ተጠቃሚዎች የሚገባቸው የዕርዳታ መጠን ለተገቢው ሰው እንደደረሰ በማረጋገጥ እና በመክፈያ ሠነዱ/በቀበሌ ስም መቆጣጠሪያ ላይ በመፈረም ለወረዳው ተወካይ ያስተላልፋል (ያጸደቀው በሚለው ሳጥን ውስጥ ወይም ድህረ ሥርጭት ማረጋገጫ ሳጥን ውስጥ ፊርማውን ማኖር አለበት)፡፡

ስርጭቱን እንዲቆጣጠር በወረዳው የተወከለው ግለሰብ ለተረጂዎች/ተጠቃሚዎች የተከፋፈለው ከስርጭት ጣቢያ መጋዘን ከወጣው ጋር መጠኑ ተመሳሳይ እንደሆነ ለማሳየት በጸደቀው የክፍያ ወይም የቀበሌ ሥርጭት ዝርዝር ሠነድ ላይ መፈረም ይኖርበታል፡፡ (ያጸደቀው በሚለው ሳጥን ውስጥ ወይም ድህረ ሥርጭት ማረጋገጫ ሳጥን ውስጥ ፊርማውን ማኖር አለበት)፡፡

በስርጭት ወቅት የጠፋ ዕርዳታ ካለ የወረዳው ተወካይ ስለ ጠፋው ዕርዳታ መቼና የት ቦታ እንደጠፋ እንዲሁም አይነትና መጠኑን ወይም የደረሰውን ጉድለት ከበቂ ምክንያት ጋር ሪፖርት ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

ተረጂዎች/ተጠቃሚዎች የሚገባቸውን ዕርዳታ በግንባር በመቅረብ ወይም በተወካዮቻቸው በኩል ካልተቀበሉ ወደ ስርጭት ጣቢያው መጋዘን እንደገና መግባቱን የሚያረጋግጥ የመረከቢያ ሠነድ ኮፒ እንዲሁም ከመከፈያ ሰነድ/የቀበሌ ስርጭት ዝርዝር ጋር ማያያዝ ይኖርበታል፡፡ (አስፈላጊ ከሆነ ወደ ስርጭት ጣቢያ መጋዘን የእርዳታ ቁሳቁስ አመላለስ ደረጃ 4 ላይ ተመልከቱ)፡፡

ማሳሰቢያ፡- በመንግስት ኦዲት መመሪያ መሰረት እና በወሩ መጨረሻ ለአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የስርጭት ሪፖርት በሚደረገው መሰረት የወረዳው ተወካይ የጸደቀውን የክፍያ/የቀበሌ ስርጭት ዝርዝር ሠነድ እና ስለ ጠፋ ዕርዳታ ሪፖርት/መረከቢያ ሠነድ ኮፒዎችን በጋራ በወረዳው ጽ/ቤት ፋይል ያደርጋል፡፡

ደረጃ 4፡ ወደ ማሰራጫ ጣቢያ መጋዘን ቁሳቁሶችን መመለስ (አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ብቻ)

በክፍያ ሠነድ/በቀበሌ ሥርጭት ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ ተረጂዎች/ተጠቃሚዎች በስርጭት ጣቢያ ካልተገኙ ወይም ዕርዳታውን እንዲረከብላቸው ሰው ካልወከሉ ስርጭቱ እንደተጠናቀቀ የሚተርፍ ዕርዳታ ይኖራል፡፡

ይህ ሁኔታ ሲከሰት ከስርጭት ጣቢያ መጋዘን የተላከው የዕርዳታ መጠን (በወጪ ሠነድ ከተመዘገበው) ለተረጂዎች/ተጠቃሚዎች ከተከፋፈለው (ክፍያ ሠነድ/የቀበሌ ሥርጭት ዝርዝር) ጋር እኩል አይሆንም፡፡ ይህ ሲሆን የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ተገቢ ነው፡-

1. ዕርዳታውን ወደ ስርጭት ጣቢያ መጋዘን ለመመለስ የመረከቢያ ሠነድ ታዘጋጃላችሁ፡፡ ከዚያም በሠነዱ ላይ አስረካቢ በሚለው ሰፍራ ላይ የተፈቀደለት አከፋፋይ (ለምሳሌ - የቀበሌው ሊ/መንበር) ፊርማውን ያኖራል፡፡ የመረከቢያው ሠነድ ኮፒ ከክፍያ ሰነድ/ የቀበሌ ሥርጭት ዝርዝር ጋር ተያይዞ በወረዳው ተወካይ አማካኝነት በወረዳው ጽ/ቤት ፋይል ይደረጋል፡፡

   ማሳሰቢያ ፡ እንዲህ አይነቱ አሰራር የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የገቢ ሪፖርት ውስጥ መካተት የለበትም፡፡ የስርጭት ጣቢያ የክምችት ሁኔታ ሪፖርት ሲዘጋጅ የተመለሰው ዕርዳታ አጠቃላይ ከስርጭት ጣቢያው መጋዘን ከወጣው ላይ መቀነስ ይኖርበታል፡፡ ተረጂዎች/ተጠቃሚዎች በመሀል መሞተው የተመደበላቸውን ዕርዳታ ካልወሰዱ በስተቀር - ደረጃ 4ን ከስር ተመልከቱ፡፡

ቁሳቁስ ወደ መጋዘን እንደገና እንደገባ ለማሳወቅ ለብቻው በመደርደር ቢን/ስቶክ ካርድ (የተዘጋጀ ከሌለ በወረቀት ላይ በመጻፍ) ታዘጋጃላችሁ፡፡ የስርጭት ጣቢያ ሌጀሩን/መዝገቡን እንደገና ማስተካከል ይኖርባችኋል፡፡

2. የተፈቀደለት አከፋፋይ (ለምሳሌ - የቀበሌው ሊ/መንበር) ዕርዳታቸውን ያልተረከቡ የተረጂዎች/ተጠቃሚዎች ስም ዝርዝር በማዘጋጀት እንዲሁም የቁሳቁሱን አይነትና መጠኑን በመመዝገብ ከእናንተ ዘንድ ይሰጣል፡፡

3. የቀበሌው ሊ/መንበር በስርጭት ጣቢያ ተገኝተው የተመደበላቸውን ዕርዳታ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለምሳሌ በአንድ ሳምንት ውስጥ መረከብ እንደሚችሉ ይጠይቃቸዋል፡፡

4. በጊዜ ገደቡ ተስማምተው ወደ ማሰራጫ ጣቢያ የሚመጡ ከሆነ የሚከተሉትን ማከናወን ይኖርባችኋል፡-

   ሀ. ዕርዳታውን ከስርጭት ጣቢያ ለማውጣት የወጪ ሠነድ በማዘጋጀት (መረከባቸውን ለማሳየት በእጅ ወይም በጣት አሻራ መፈረም በቡድን ከመጡ ደግሞ በተወካያቸው አማካኝነት) ያረጋግጣሉ፡፡

   ማሳሰቢያ ፡- የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የክምችት ሁኔታ ሪፖርት ሲዘጋጅ ከስርጭት ጣቢያ ከሚወጣው ጋር እንደገና ተደምሮ ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡ በተጨማሪም ወደ ወረዳ ከሚላከው ሪፖርት ጋር የስርጭት ጣቢያ የወጪ ሠነድ ቅጅ ተያይዞ መላክ ይኖርበታል፡

   ለ. የቀበሌ ሊ/መንበሩ ባዘጋጀው የስም ዝርዝር ላይ እያንዳንዱ ተረጂ በእጁ ወይም በጣት አሻራ እንዲፈርም ትጠይቃላችሁ፡፡

ተረጂዎቹ የሚገባቸውን እርዳታ ተረክበው እንደጨረሱ ወይም የመረከቢያ ቀን ገደቡ እንዳለፈ ዝርዝራቸውን ለወረዳው መላክ ይኖርባችኋል፡፡ የሚተርፍ ዕርዳታ ቢኖር የወረዳው ንብረት ተደርጎ ይቆጠርና በወደፊት ሥርጭት ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል፡፡

5




የመርሃዊ ሪፖርት አዘገጃጀት

5 የወርሃዊ ሪፖርት አዘገጃጀት

የአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የእርዳታ ቁሳቁሶች ላይ ብቻ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ፡፡

ምስል 6፡ የወርሃዊ ሪፖርት አዘገጃጀት የስራ ሂደት ደረጃዎች



በኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር መሰረት ወር በገባ በመጀመሪያዉ ቀን ሃላፊ ለሆናችሁበት የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ለሚያሟላ ለእያንዳንዱ ስርቄት ጣቢያ ወርሃዊ የክምችት ሁኔታ ሪፖርት ታዘጋጃላችሁ ፡-

- ባለፈው ወር በመጀመሪያና በመጨረሻ ቀናት ውስጥ የእርዳታ ቁሳቁሶችን ተረክባችሁ ከሆነ ወይም ፤
- ባለፈው ወር በመጀመሪያና በመጨረሻ ቀናት ውስጥ ተከማችቶ የሚገኝ ቁሳቁስ ካለ ወይም ፤
- ባለፈው ወር በመጀመሪያና በመጨረሻ ቀናት ውስጥ ከመጋዘን ወጪ የተደረገ ቁሳቁስ ካለ ፡፡

ማንኛውም የስርጭት ጣቢያ ባለፈው ወር በወሩ መጀመሪያና መጨረሻ ቀናት ውስጥ ገቢ የተደረጉ የእርዳታ ቁሳቁሶችን በተመለከተ የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የገቢ ሪፖርት ማዘጋጀት አለባችሁ፡፡(ከላይ የመጀመሪያዉን ቅድመ ሁኔታ ተመልከቱ)

የሴፍቲኔት እና የዕለት ዕርዳታ ፕሮግራም ቁሳቁሶች በተመሳሳይ የሪፖርት ወር ውስጥ በአንድ የስርጭት ጣቢያ ገቢ ቢሆኑ ለእያንዳንዱ ፕሮግራም የየራሱ የስርጭት ጣቢያ የክምችት ሁኔታ ሪፖርትና ወርሃዊ የስርጭት ጣቢያ የገቢ ሪፖርት በተለያየ ጥራዝ መዘጋጀት አለበት፡፡ ላልታሰበ ድንገተኛ አደጋ የዕለት እርዳታን ጥራዝ በመጠቀም ለብቻው ሪፖርት መዘጋጀት አለበት፡፡

- ቆጠራ አካሂዳችሁ የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ ሪፖርት ለማዘጋጀት እንድትችሉ በኢትዮጵያ አቆጣጠር በወሩ የመጀመሪያ ቀን ጠዋት ስርጭት ላይካሄድ ይችላል፡፡

- በወሩ የመጀመሪያ ቀን አሽከርካሪው በስርጭት ጣቢያ ለማራገፍ ከተገኘ ወርሃዊ ቆጠራችሁን እና የስርጭት ጣቢያ ሪፖርት አዘጋጅታችሁ እስከምትጨርሱ ድረስ መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

ደረጃ 1: የስርጭት ጣቢያውን ወርሃዊ የክምችት ሁኔታ ሪፖርት ማዘጋጀትና እና ቆጠራ ማካሄድ

በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን የስርጭት ጣቢያ የክምችት ሁኔታ ሪፖርት ማዘጋጀት ይኖርባችኋል፡፡

ሪፖርቱ የሚጠናቀረው በስርጭት ጣቢያ መዝገብ ላይ በመመስረት ሲሆን ለማረጋገጥ በመጋዘን የሚገኘውን ቁሳቁስ መቁጠር አለባችሁ፡፡ የቆጠራው ውጤት በመዝገብ ላይ ከሰፈረው ጋር ልዩነት ካሳየ ምርመራ በማካሄድ ሌጀሩን/ መዝገቡን ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

በመጋዘን የሚገኘው ክምችት ከስርጭት ጣቢያ ሌጀር ጋር ትክክል መሆኑን ካመናችሁበት የወሩን ከወጪ ቀሪ በነጠላና በብዛት በሌጀሩ ላይ በመጻፉ ስራው መጠናቀቁን ለመግለጽ በመፈረምና ቀኑን በመጻፍ ማረጋገጥ ይኖርባችኋል፡፡

ማሳሰቢያ ፥ የስርጭት ጣቢያው ቋሚ ከሆነ የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የክምችት ሁኔታ ሪፖርት በዚያው ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ቋሚ ካልሆነ ግን በወረዳው ጽ/ቤት መቀመጥ አለበት፡፡

በስርጭት ጣቢያ ለሚገኙ ለእያንዳንዱ የዕርዳታ ቁሳቁስ አዲስ ወር እንደተጀመረ በስርጭት ጣቢያ መዝገብ ላይ በአዲስ ገፅ መጀመር/መጻፍ ይኖርባችኋል፡፡ ይህ አሰራር በቀላሉ የእያንዳንዱን ወር ሪፖርት ለማዘጋጀት ይረዳችኋል፡፡

ደረጃ 2: የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የገቢ ሪፖርት ላይ መፈረም

የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የገቢ ሪፖርት ላይ ላለፈው ወር በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን መፈረም አለባችሁ፡፡

ማሳሰቢያ ፥ ላለፈው ወር ወደ ስርጭት ጣቢያ ዕርዳታ ገቢ እንደተደረገ ሪፖርቱ ደረጃ በደረጃ መሟላት አለበት፡፡

በስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የክምችት ሁኔታ ሪፖርትና በሌጀሩ መረጃ መሰረት ገቢ የተደረጉት የዕርዳታ ቁሳቁሶች ድምር ከጠቅላላው ድምር ጋር እኩል መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባችሁ፡፡

ማሳሰቢያ ፥ የስርጭት ጣቢያው ቋሚ ከሆነ የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የገቢ ሪፖርት በዚያው ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ቋሚ ካልሆነ ግን በወረዳው ጽ/ቤት መቀመጥ አለበት፡፡

ደረጃ 3: የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ ሪፖርቶችን ወደ ወረዳ መላክ

2 በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የክምችት ሁኔታ እና የገቢ ሪፖርቶችን ከተረጋገጠና ከተፈረመበት በኋላ ወደ ወረዳው ትልካላችሁ፡፡

የመጨረሻውን ኮፒ በጥራዙ ላይ በማስቀረት የእያንዳንዱን ሪፖርት ኦርጅናልና ሁሉንም የካርቦን ቅጅዎች ወደ ወረዳው መላክ ይኖርባችኋል፡፡

! ሪፖርቱ ወደ ወረዳ ለመድረስ ስለሚፈጅበት አጠቃላይ ጊዜ (ወደ ወረዳው ጽ/ቤት ሪፖርቱ ለመድረስ የሚፈጀው ቀናት) ካርድ ቁ. 2 ተመልከቱ፡፡

3 የእርዳታ ቁሳቁሶቹ ገቢ በሚደረጉበት ወቅት ተያያዥነት ያላቸዉ የመረከቢያ ሰነዶች ለወረዳው ካልተላኩ በሪፖርት ወቅት ከሪፖርቶቹ ጋር ተያይዘው መላክ ይኖርባቸዋል፡፡ የተሻሻለውን የክልል ቅጽ ቅጅዎችን ማሰራጫ መመሪያዎች በካርድ ቁ. 3 ተመልከቱ፡፡

የወረዳው ባለሙያ የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ ሪፖርቶችን በመገምገም የወረዳውን ሪፖርት ያዘጋጃል

የወረዳውን ወርሃዊ ሪፖርት ለማዘጋጀትና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ የእያንዳንዱን ስርጭት ጣቢያ እና ፕሮግራም የተረጋገጠ ስለመሆኑ የወረዳው ባለሙያ የእያንዳንዱን የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ ሪፖርቶች ይገመግማል፡፡

1. **የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የገቢ ሪፖርት** ውስጥ የተገለጸው ጠቅላላ የእርዳታ ቁሳቁስ ገቢ ድምር **ከስርጭት ጣቢያ የክምችት ሁኔታ ወርሃዊ ሪፖርት** ውስጥ ከተገለጸው ጠቅላላ የገቢ ድምር ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት፡፡
2. በስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የገቢ ሪፖርት ውስጥ ለእያንዳንዱ ገቢ **መረከቢያ ሰነድ** ሲኖር ተከታታይ ቁጥር ያላቸውን የመረከቢያ ሰነድ ይጠቀማሉ፡፡

3. በእያንዳንዱ የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የክምችት ሁኔታ ሪፖርት ውስጥ የወሩ መጀመሪያ ከወጪ ቀሪ ከባለፈው ወር የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የክምችት ሁኔታ ሪፖርት ከወሩ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት ፡፡ ይህም እንደሚከተለው ይቀርባል

የወሩ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ = የወሩ መጀመሪያ ከወጪ ቀሪ + በወሩ ውስጥ ገቢ የተደረጉ - በወሩ ውስጥ የተሰራጩ - በወሩ ውስጥ የተበላሹ/የጠፉ

4. በእያንዳንዱ ስርጭት ወቅት የተቆረጠው የስርጭት ጣቢያ ተከታታይነት ያላቸውን የወጪ ሠነዶችን መጠቀም ፡፡

ወጪ የተደረጉ/የተላኩ ዕርዳታዎች = የስርጭት ጣቢያው የወጪ ሠነዶች ድምር + ወጪ ከሆኑ በኋላ እንደገና ወደ መጋዘን ተመላሽ የተደረጉ ገቢ ደረሠኞች ድምር ነው *

*እንደገና ገቢ የተደረጉ ደረሠኞች ተረጂዎች/ተጠቃሚዎች በወቅቱ ባለመቅረባቸው ከስርጭት በኋላ እንደገና ተመልሰው የመረከቢያ ሰነድ ተቆርጦላቸው ወደ መጋዘን ገቢ የተደረጉ ናቸው ፡፡

5. ደሞዝ መክፈያዎች/የቀበሌ ሥርጭት ዝርዝሮች ከዚህ በታች የተመለከተውን ማረጋጥ ይኖርባቸዋል ፡-

ወጪ የተደረጉ ዕርዳታዎች = የተሰራጩ ድምር + በስርጭት ወቅት የጠፉ + ወጪ ከሆኑ በኋላ እንደገና ወደ መጋዘን የተመለሱ ድምር ነው

ማንኛውንም ልዩነት ፣ የጠፉ መረከቢያ ሰነዶች ወይም የጠፉ የስርጭት ጣቢያ የወጪ ማዘዣ ሰነዶችን በመመርመር በአስቸኳይ ማስተካከል ይገባል ፡፡


6



ሣምንታዊ የቁሳቁስ ቁጥጥር እና ፍተሻ

6 ሣምንታዊ የቁሳቁስ ቁጥጥር እና ፍተሻ

ምስል 7፡ - የእርዳታ ቁሳቁስ ፍተሸ/ ቁጥጥር አሰራር ሂደት ደረጃዎች



ይህ አሰራር ተግባራዊ የሚሆነው የዕርዳታ ቁሳቁሶቹ በመጋዘን ውስጥ ከአንድ ሳምንትና ከዚያ በላይ ከተከማቹ ነው፡፡ በአንድ የምደባ ዙር/ወር ድልድል ወቅት የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ዕርዳታ ሲራገፍ የጊዜ ክፍተት ካለው እንደ መደበኛው የአሰራር ፍሰት ታስቦ ይከናወናል፡፡


በዚህን ጊዜ ከዚህ በታች በተገለጸው አሰራር መሰረት ሳምንታዊ ምርመራ ማካሄድ ይኖርባችኋል፡፡

ደረጃ 1: የእርዳታ ቁሳቁሱን ደህንነት በየሳምንቱ መፈተሽ

ችግሮች ሲከሰቱ አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችል ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ የመጋዘን ምርመራ ታካሂዳላችሁ ፡፡

ከረጢቶቹ የተቀደዱ ፣ በውኃ ምክንያት የተበላሹ ወይም የተሰረቁ እንዳሉ ሁሉንም የዕርዳታ ቁሳቁሶች ትፈትሻላችሁ ፡፡

ነፍሳትና አይጦች መኖራቸውን የተበላሹ ዕህሎችን እና እዳሪያቸውን በማየት ፣ በመስማትና በማሽተት ታረጋግጣላችሁ ፡፡




የጠንዚዛ ፣ የብል ፣ የሸረሪት ድርና የዕጭ ምልክቶች



በወፎችና በአይጦች የተበላ ከረጢት




ከላይ ያለውን ከረጢት በማንሳት የታችኛውን ከረጢት ሙቀት በእጅ መለካት



የተበሱና የተቀደዱ ከረጢቶች

የዕርዳታ ዕህሉን በናሙና መውሰጃ ወስፋ እንድትወስዱ ከታዘዛችሁ መሳሪያውን በመጠቀም ናሙና መውሰድ ትችላላችሁ ፡፡ የወሰዳችሁትን ናሙና በማሽተትና በመመልከት የመንቀዝ ወይም የመሻገት ምልክት እንደሌለው ታረጋግጣላችሁ ፡፡








የናሙና መውሰጃ ወስፌ አጠቃቀም

በንፍሳት የተጎዳ ከረጢት

በወረቀት ከረጢት የታሸጉ ዱቄቶችና ቅይጥ ምግቦችን ተመሳሳይ ዘዴዎችን በመጠቀም ድርድሩን መፈተሽ ይኖርባችኋል፡፡ ነገር ግን ከረጢቱ ሊቀደድ ስለሚችል በናሙና መውሰጃ ወስፌ መውጋት የለባችሁም፡፡


በወረቀት የታሸጉ የዱቄት ወተቶች አንዳንድ ጊዜ ሊጠጥሩ ይችላሉ፡፡ በእጅችሁ በመነካካት አለመጠጠሩን ማረጋገጥ ይኖርባችኋል፡፡	
በጣሳ የታሸጉ አይብ፣ ስጋና አሳዎችን የታሸጉበትን ካርቶን በመክፈት የመዛግ እና የማበጥ ምልክት ይታይባቸው እንደሆነ ውጫዊ ክፍላቸውን በማየት ማረጋገጥ አለባችሁ ፡፡	

የምግብ ዘይቶች መያዣዎቻቸው አለማንጠባጠባቸውን በመመልከት ማረጋገጥ



ፍተሻው ከየትኛው ስፍራ ይጀመር

ድርድሩን በሁሉም አቅጣጫ መፈተሽ (ነፍሳት አለመኖራቸውን በማዳመጥ ማረጋገጥ)፡፡







በተለምዶ ነፍሳት ከብርሀን ይደበቃሉ፡፡ በከረጢቶች መካከል ፣ በመገጣጠሚያ ስፍራና በመያዣ አካባቢዎች በመመልከት አለመኖራቸውን ታረጋግጣላችሁ፡፡



በማዕዘን አካባቢዎች ለመመልከት ከረጢቶችን በከፊል በማንሳት አሰረዝሞ መመልከት፡፡



ከድርድሩ አናት ላይ በመሆን የተወሰኑ ከረጢቶችን በማንሳት የታችኛውን ክፍልና የድርድሩን መሰረት ዙሪያና ከመደርደሪያው ስር በመመልከት ነፍሳትና የአይጦች ጥቃት ምልክት እንደማይገኝ ማረጋገጥ፡፡



በደንብ የሚያበራ የእጅ ባትሪ በመጠቀም ጨለማ ቦታዎችን መፈተሽ ፡፡


የሚከተሉትን ምርመራዎች በግል ማካሄድ ይኖርባችኋል ፡-

- የሚያንጠባጥብ ጣሪያ ፣
- የተሰበረ መስኮት ወይም አየር ማስተላለፊያ ፣
- የማይገጥሙ በሮች ፣
- የተሰነጠቁ ግድግዳዎች እና ወለሎች ፣
- የአይጥ ጉድጓድ ምልክቶች ፣

የውጭ ክፍልና ግቢውን በመፈተሽ ማረጋገጥ ይኖርባችኋል ፡፡

በምርመራ ወቅት ያጋጠማችሁን በመመዝገብ የመጋዘን ምርመራ ሪፖርት ስታዘጋጁ ምርመራው መቼ እንደተካሄደ መጥቀስ አለችሁ ፡፡





መረጃውን በማስታወሻ ደብተር በመያዝ ወይም በድርድሩ ላይ በሚገኘው ቢን ካርድ ወይም በግድግዳው ላይ ማንጠልጠል ይኖርባችኋል ፡፡ ይህም የተከማቸው የዕርዳታ ሁኔታ ቁሳቁስና መጋዘኑ አንድ የምርመራ ወቅት ከሌላው የምርመራ ወቅት ምን መሻሻል እንደተደረገ ያሳያል ፡፡

የተበላሹ ነገሮች ካጋጠማችሁ ከዚህ በታች በተዘረዘረው አሰራር መሰረት ማከናወን ይጠበቅባችኋል ፡፡ ምላሽ ያላገኙ ችግሮች ቢኖሩ የቅርብ አለቃችሁን አመራር ትጠይቃላችሁ ፡፡

ማሳሰቢያ፥ የተለመደው ሳምንታዊ ምርመራ በሚካሄድበት ጊዜ በቂ የሆኑ አስገዳጅ ቅጾች መኖራቸውን እና ለመጋዘን የሚያገለግሉ መሰረታዊ መሳሪያዎች ክፍል 7፥ የስርጭት ጣቢያ ከባቢያዊ ሁኔታ ዉስጥ በተዘረዘሩት መሰረት በአቅራቢያችሁ መኖራቸውን ማረጋገጥ ይሮርባችኋል፥፥ የጠፉ ዕቃዎችን ለቅርብ አለቃችሁ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባችኋል፥፥



በስርጭት ጣቢያ ደረጃ የመጋዘን ሰራተኛው ለመጠቀም የሚያስችል በኢትዮጵያ መንግስት የጸደቁ አስገዳጅ ቅጾች ዝርዝር ከዚህ በታች የተገለጹ ሲሆን በተጨማሪም ካርድ ቁ. 1 ውስጥ ይገኛሉ፥፥

ደረጃ 2: የመጋዘኑን ቆሻሻዎች ማስወገድ

በሳምንታዊ የመጋዘን ምርመራ መሰረት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መሰረት ቆሻሻዎችን ማስወገድ ይኖርባችኋል፥፥

የሚያንጠባጥቡና የፈሰሱ ነገሮች

- በንጹህ ወለል ላይ የፈሰሱ ጥራጥሬዎችና ቦሎቄዎች እንደ ቆሻሻ አይቆጠሩም ፤ እንደ አስፈላጊነቱ በወንፊት በማጣራት እንደገና ማሸግ ያስፈልጋል፥፥ ነገር ግን አነስተኛና ቆሻሻ ከሆነ መወገድ አለበት፥፥

- በወለሉ ላይ የፈሰሱ ዱቄትና ቅይጥ ምግቦች ከሆኑ ግን በተለመደው መንገድ መወገድ ያኖርባችኋል፥፥

- የፈሰሱ ዕህሎች ለነፍሳት ምቹ መራቢያ ስፍራ ስለሚሆናቸውና ከዚያም ወደ ድርድሩ በመዛመት የተከማቸውን ቁሳቁስ ሊያበላሹ ስለሚችሉ በአካባቢው መመሪያ መሰረት ጥራጊዎችና ሌሎች ቆሻሻ ነገሮች በሙሉ በተቻለ ፍጥነት መወገድ ይኖርባቸዋል፥፥



ቆሻሻዎችን ከመጋዘኑ ራቅ አድርጎ ማቃጠል

የተበላሹ ቁሳቁሶች

ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች በመጋዘን የሚገኙ ዕህሎች ለምግብነት ተስማሚ ላይሆኑ ይችላሉ ፡፡ ለምሳሌ

- የሻገተ ፣ የሞቀ ወይም በወረርሽኝ የተጠቃ ዕህል ከሆነ ፣
- የሞቀ የወተት ዱቄት ፣
- የዛጉ ፣ የሚያንጠባጥቡ ወይም ያበጡ ጣሳዎች ፣
- የአሲድነት/የተለየ ሽታ ያላቸው የምግብ ዘይቶች ፣

እነዚህን የመሳሰሉ ችግሮች ሲከሰቱ ወዲያዉኑ ለቅርብ አለቃችሁ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባችኋል ፡፡ በሚጠናቀረው ሪፖርት ውስጥ ስለተበላሸው የምግብ አይነት ፣ የትኛው የዕርዳታ ቁሳቁስ ሲጓጓዝ ችግሩ እንደተከሰተ ፣ የተበላሸው የዕርዳታ ቁሳቁስ መጠንና የጉዳቱ አይነት መጠቀስ ይኖርበታል ፡፡

የቅርብ አለቃችሁ የተበላሸውን ዕህል ለመመርመርና እንዲወገድ ውሳኔ ለማስተላለፍ ከሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች የተውጣጣ ጊዜያዊ ኮሚቴ ማቋቋም ይኖርበታል ፡፡ አላግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል (ገበያ ላይ እንዳይውል) ለመከላከል በሚዋቀረው ኮሚቴ ውስጥ የፖሊስ ተጠሪ ቢኖር መልካም ነው ፡፡

የተበላሸ ምግብ ከሌሎቹ ተለይቶ ለብቻው መቀመጥ ይኖርበታል ፡፡ ቢቻል ከዋናው መጋዘን ወጥቶ በሌላ ስፍራ ቢቀመጥ ይመረጣል ፡፡ የተበላሸውን የዕርዳታ ቁሳቁስ በስርጭት ጣቢያ ሌጀር/መዝገብ ፣ በቢን ካርድ ላይ (የሚጠቀሙ ከሆነ) መመዝገብ አስፈላጊ ነው ፡፡

በከፍተኛ ሁኔታ በወረርሽኝ የተጠቃ ምግብን ተጨማሪ ጉዳት እንዳያደርስና ወደሌሎች እንዳይዛመት ለመከላከል ማከም አስፈላጊ ነው ፡፡ የተባይ መከላከያ መድኃኒት በባለሙያ ማስረጨት አስፈላጊ ነው ፡፡ የሚቻል ከሆነ ለተባይ መከላከያ ቡድን ጥሪ ብታደርጉ መልካም ነው ፡፡

የተበላሹ የዕርዳታ ቁሳቁሶችን ለማስወገድ ግልጽ የሆነ መመሪያ ከቅርብ አለቃችሁ መመሪያ ካልደረሳችሁ በስተቀር ማስወገድ የለባችሁም ፡፡ አስፈላጊው መመሪያ እንደደራስችሁ ወዲያውኑ ማስወገድ ያስፈልጋል ፡፡ አንዳንድ የሚወገዱ ዕህሎች ለከብቶች ተስማሚ ሊሆኑ ይችላሉ ፡፡ ነገር ግን ለማረጋገጥ የቤተ-ሙከራ ምርመራ ያስፈልጋል ፡፡

ማሳሰቢያ ፡- የሚወገዱ ቁሳቁሶች ሙሉ በሙሉ እስካልተወገዱና ከሰርጭት ጣቢያ መጋዘን ሌጀር/መዝገብ እና ቢን ካርድ ላይ (የሚጠቀሙ ከሆነ) እስካልተቀናነሱ ድረስ የእናንተ ኃላፊነት ይሆናል ፡፡

የመያዣ ዕቃዎችን ማከማቸትና ማስወገድ

ባዶ ከረጢቶች ፣ ካርቶኖች ፣ ጣሳዎች ፣ ጠርሙሶችና በርሜሎች ለአይጦችና ለነፍሳት የመደበቂያ ስፍራ እንዳይሆኑ በጥንቃቄ መቀመጥ ይኖርባቸዋል ፡፡

የሚቻል ከሆነ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ ፡

- ከረጢቶችን በማራገፍ ርጋፊዎችን ማፅዳት ፣
- ጣሳዎቹ ፣ጠርሙሶቹና በረሜሎቹ ላይ መክደኛዎቻቸው በትክክል መገጠሙን ማረጋገጥ ፣
- የታጠፉ ካርቶኖችን መዘርጋት ፣

የቅርብ አለቃችሁ የባዶ ኮንቴይነሮች አወጋገድ መመሪያ መስጠት ይጠበቅበታል ፡፡ እንደገና ለመጠቀም የማያገለግሉ ከሆነ በተቀመጠው መመሪያ መሰረት ለሽያጭ ማቅረብ ፡፡

ደረጃ 3: የዕርዳታ ቁሳቁሶች እንዳይበላሹ መቆጣጠር

በመጋዘን የሚገኙት ቁሳቁሶች እንዳይበላሹ (ብልሽትን ለመቀነስ) አስፈላጊውን እርምጃ ትወስዳላችሁ ፡፡ ከፍተኛ ጥፋት የሚደርሰው በተባይ ወረርሺኝ እና/ወይም በእርጥበት ምክንያት ነው ፡፡ በሚከተሉት መንገዶች የዕርዳታ ቁሳቁሱን ብልሽት መቀነስ ይቻላል ፡-

1. የስርጭት ጣቢያ መጋዘን ውጫዊና ውስጣዊ ክፍሎች ጽዳት መጠበቅ ፣
2. በስርጭት ጣቢያ መጋዘን ቆይታቸውን መቀነስ ፣
3. የስርጭት ጣቢያ መጋዘኖችን ከዝናብና ከጎርፍ መከላከል ፣
4. የተባይ ወረርሽኝን ለመቆጣጠር አስቸኳይ ዕርምጃ መውሰድ ፡፡

እንደ ጉዳቱ መንስኤ አይነት ጉዳትን ለመቆጣጠር የሚወሰዱ የተለያዩ ዘዴዎች ይገኛሉ ፡
፡ ከዚህ በታች የተቀመጠው ሠንጠረዥ ለተለያዩ ጉዳቶች በተወሰኑ ሁኔታዎች ሊወሰዱ የሚገቡ ዕርምጃዎችን በማጠቃለያ መልክ ያቀርባል ፡፡

ሠንጠረዥ 1 - የዕርዳታ ቁሳቁሶችን ብልሽት ለመቀነስ ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎች

የጉዳት ዓይነት	የጉዳት ምልክት	የመቆጣጠሪያ ዘዴዎች	የሚወሰዱ ዕርምጃዎች
ክብደታቸው የቀነሰ መያዣዎች	■ ከረጢቱ የተጨማደደ ከሆነ ■ መያዣ እቃው ሲያነሱት የሚቀል ከሆነ ■ ክብደታቸውን ለመመዘን በናሙናነት የተመዘኑ ከረጢቶች መቅለላቸው ከታወቀ	■ በሚራገፉበትና በሚከፋፈሉበት ወቅት የጥበቃውን ሁኔታ ማጠናከር ■ ከፍተኛ መጠን ያላቸው ቁሳቁሶች ሲሆኑ በከረጢት ሲሞሉ የጥበቃውን ሁኔታ ማጠናከር	■ እንደገና ማሸግ ወይም ክብደቱን ማስተካከል ■ ስለ ተበላሸው ቁሳቁስ ሪፖርት ማዘጋጀት ■ በሰርቄት ጣቢያ ሌጀር/መዝገብ ላይ መመዝገብ
የሚያንጠባጥቡ ፣ የተበሱ ወይም የተቀደዱ መያዥያዎች	■ የተረፈው/ዝቃጩ በቄነት መኪናው ላይ ይቀራል ■ በሚራገፍበት ወቅት ምግቡ ይንጠባጠባል ■ ከረጢቱ የተቀደደ እና መያዣዎቹ የተጨማደዱ ወይም የተጨፈለቁ ሆነው ይታያሉ	በጥንቃቄ መያዝ፡- ■ አለመወርወር ■ ድርድሩን በጣም ከፍ አለማድረግ ■ መንጠቆዎችን አለመጠቀም ■ ወለል ላይ አለመጎተት ■ የታሸገበት እቃ በቂ ሆኖ ካልተገኘ ለፕሮግራም ባለሙያው ማሳወቅ	■ ለመመገብ ተስማሚ የሆነውን እንደገና ማሸግ ■ ጥራጊውን በመመርመር እንደገና ማሸግ ወይም ለምግብነት ተስማሚ ያልሆነውን በማረጋገጥ ማስወገድ ■ ስለ ተበላሸው ቁሳቁስ ሪፖርት በማዘጋጀት መረጃውን ማስተካከል

የጉዳት ዓይነት	የጉዳት ምልክት	የመቆጣጠሪያ ዘዴዎች	የሚወሰዱ ዕርምጃዎች
የረጠበ ፣ የዛገ ወይም የሻገተ ከረጢት ወይም መያዥያ	■ ሲይዙት የረጠበ ወይም የሚያንጠባጥብ መያዣ ■ ቀለማቸው የተቀየሩ መያዣዎች ■ ያልተለመደ ሽታ (የሻገተ ወይም የኬሚካል) ■ የበሰለ ምግብ ሽታ	■ በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖር ማድረግ ■ በማሸጊያ ላይ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን በመጋዘን አለማከማቸት (የተለየ ፈቃድ ተያይዞ ካልመጣ በስተቀር) ■ ከመጋዘን ውጪ ሲከማቹ በመሸፈኛ ማስቀመጥ ■ ያለ በቂ መሸፈኛ የዕርዳታ ቁሳቁሶቹ ተጓጉዘው ከሆነ ለፓሮግራም ባለሙያው ሪፓርት ማድረግ ለምሳሌ፥ የዝናብ መከላከያ ሸራ ፣ ውሃ የማያስገባ መሸፈኛ ሸራ	■ ለምግብነት ተስማሚ የሆነውን በመመርመር እንደገና ማሸግ ■ ለምግብነት ተስማሚ ያልሆነውን በማረጋገጥ ማስወገድ (በፕሮግራም ባለሙያው አማካኝነት) ■ በዝናብ የረጠበ ምግብ ከሆነ በማድረቅ ለምግብነት እንዲውል ማድረግ ■ ስለ ተበላሸው ቁሳቁስ ሪፓርት ማዘጋጀት የስርጭት ጣቢያ ሌጀር/ መዝገብ ማስተካከል
ያበጡ ወይም የዛጉ ጣሳዎች	■ የማሸጊያውን ውጫዊ አካል በተለይ መጋጠሚያውና የታሸገበት አካባቢ መዛግ ■ መያዥያው ሲያብጥ ወይም ቅርጽ የለሽ ሲሆን	■ በቀጥታ የፀሐይ ብርሀን በሚያገኝበት ስፍራ አይቀመጥ ■ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ከአራት ወራትና ከዚያ በላይ ያለፈባቸውን በመጋዘን አለማስቀመጥ (የተለየ ፈቃድ ተያይዞ ካልመጣ በስተቀር)	■ ለምግብነት ተስማሚ የሆነውን በመመርመር እንደገና ማሸግ ■ ለምግብነት ተስማሚ ያልሆነውን በማረጋገጥ ማስወገድ ■ ስለ ተበላሸው ቁሳቁስ ሪፓርት ማዘጋጀት የስርጭት ጣቢያ ሌጀር/ መዝገብ ማስተካከል
በአይጦች ወይም በወፎች የተወረረ	■ አይጦችና ወፎች በመጋዘን ውስጥ ይታያሉ ■ እዳሪያቸው በወለል ወይም በድርድሩ ላይ ይታያል ■ የተበሉ ከረጢቶች ወይም መያዣዎች ይኖራሉ ■ በአዉራ ላይ ዱካቸው ይታያል ■ የወፍ ጎጆዎች መኖር	■ የመጋዘኑን ዕዳት ሁልጊዜ መጠበቅ (ውስጡንና ውጪውን ማጽዳት) ■ ጉድጓዶችን ወይም በግድግዳ ፣ በወለልና በጣሪያ ላይ የሚታዩ ቀዳዳዎችን መድፈን ■ በመስኮቶችና በአየር ማስገቢያዎች ላይ ወንፊቶችን ማኖር ■ በመጋዘኑ የውስጥ ክፍል የአይጥ ወጥመዶችን ማኖር ነገር ግን የአይጥ መርዝ መኖር የለበትም፥፥ ■ ባሕላዊ ዘዴዎችን መጠቀም (ጭስ) ■ መከላከያ መሳሪያዎችን መጠቀም (ወጥመድ ፣ ድምጹ የሚረብሽ መሳሪያ) ■ የሚገኝ ከሆነ የኬሚካል መከላከያዎች	■ ለምግብነት ተስማሚ የሆነውን በማረጋገጥ እንደገና ማሸግ ■ ለምግብነት ተስማሚ ያልሆነውን በማረጋገጥ ማስወገድ ■ ስለ ተበላሸው ቁሳቁስ ሪፓርት ማዘጋጀት እና የስርጭት ጣቢያ ሌጀር/ መዝገብ ማስተካከል

የጉዳት ዓይነት	የጉዳት ምልክት	የመቆጣጠሪያ ዘዴዎች	የሚወሰዱ ዕርምጃዎች
የተባይ ወረርሽኝ መኖሩ	■ በራሪ ነፍሳት ■ በሕይወት ያሉ ወይም የሞቱ ነፍሳት ■ ዕጮች ■ በአዟራው ላይ የሚታይ የነፍሳት ወይም የእጭ ምልክት ■ የዕህል ከረጢቱ ጥቃቅን ቀዳዳዎችና ብዛት ያለው አዟራ ሲታይ ■ ከከረጢቱ ውስጥ ድምጽ ሲሰማ ■ በጥራጥሬው ወይም በቦለቄው ውስጥ ቀዳዳዎች ሲኖሩ ■ ሀይለኛ ሽታ የሚያመነጭ ከሆነ	■ የመጋዘኑን ፅዳት ሁልጊዜ መጠበቅ (የውስጠኛውንና የውጨውን ከፍል ማጽዳት) ■ ከአዟራና ከፍርስራሽ ነፃ ማድረግ ■ በወረርሺኝ የተጠቃውን ቁሳቁስ ካልተጠቃው ጋር በጋራ አለማስቀመጥ	■ በመመርመር የሚቻል ከሆነ መድኃኒት መርጨት ■ ለምግብነት ተስማሚ ያልሆነውን በማረጋገጥ ማስወገድ ■ ስለ ተበላሸው ቁሳቁስ ሪፖርት ማዘጋጀት እና የሰርጭት ጣቢያ ሌጀር/መዝገብ ማስተካከል
ጥራጊ	■ ከተበላው ወይም ከተጨማደደው ከረጢት ምግብ ሲንጠባጠብ ■ እንደገና ከታሸገው ከረጢት ምግብ ሲንጠባጠብ	■ ተገቢ ያልሆነ አያያዝን ማስወገድ ■ ዕቃዎቹን በተደጋጋሚ ማንቀሳቀስ መተው ■ እንደገና በሚታሸግበት ወቅት ተጨማሪ ብክነት እንዳይኖር ለወዛደሮቹ መመሪያ መስጠት	■ ፅዳቱን ለመጠበቅ በተደጋጋሚ ወለሉን መጥረግ ■ ለምግብነት ተስማሚ የሆነውን በማረጋገጥ እንደገና ማሸግ ■ ጥራጊዎቹ ለምግብነት ተስማሚ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ■ ስለ ተበላሸው ቁሳቁስ ሪፖርት ማዘጋጀት እና የሰርጭት ጣቢያ ሌጀር/መዝገብ ማስተካከል

ምንጭ ፥ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች አስተዳደር መመሪያ (የአማራ መልሶ ማቋቋምና ልማት ድርጅት (አመልድ) 2005 እአአ)

በመጋዘን ውስጥ የጠፉ የዕርዳታ ቁሳቁሶች ካሉ ስለ ጠፉ ቁሳቁሶች መቼ እና የት ቦታ እንደጠፉ እና የጠፋው ወይም የተበላሸ ዕርዳታ ብዛትና አይነት ዝርዝር ከነምክንያቱ

በሪፖርት ማዘጋጀት ይኖርባችኋል፡፡ በፅሁፍ ተዘርዝሮ አንደኛው ቅጅ በስርጭት ጣቢያ መዝገብ ጋር ሲያያዝ ሌላኛው ኮፒ ለቅርብ አለቃችሁ ይላካል፡፡



በመጋዘን እያሉ የጠፉ ወይም የተበላሹ የዕርዳታ ቁሳቁሶች ካሉ በሪፖርት መልክ በፅሁፍ ተዘርዝሮ አንደኛው ቅጅ ከስርጭት ጣቢያ መዝገብ ጋር ሲያያዝ ሌላኛው ኮፒ ለወረዳ ይላካል፡፡

ደረጃ 4: መጠነኛ የመጋዘን ጥገና ማካሄድና ለተጨማሪ ጥገና ለቅርብ አለቃ ማሳወቅ

በሳምንታዊ የስርጭት ጣቢያ መጋዘን ምርመራ ወቅት አስፈላጊ ጥገና የሚያስፈልጋቸው ነገሮች ካጋጠሟችሁ የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅባችኋል፡-

1. መጠነኛ የጥገና ስራዎች ከሆኑ በእናንተ መከናወን የሚያስችሉ መሳሪያዎች ካሉ ወዲያውኑ መጠገን (በክፍል 7፣ የስርጭት ጣቢያ መጋዘን ከአካባቢያዊ ሁኔታ የሚለውን ተመልከቱ) ፣

2. ከፍተኛ ጥገና የሚያስፈልገው (ከእናንተ አቅም በላይ) ከሆነ ለቅርብ አለቃችሁ አሳውቁ፡፡

መጠነኛ የመጋዘን ጥገና እንደሚከተለው ይተረጎማል፡፡ ያለተጨማሪ በጀት በስርጭት ጣቢያ በሚገኝ የመጠገኛ መሳሪያ አማካኝነት በመጋዘን ሠራተኛው አቅም የሚጠገን ነው፡፡

7



የስርጭት ጣቢያ መጋዘን አጣቢያዊ ሁኔታ

7 የስርጭት ጣቢያ መጋዘን ከባቢያዊ ሁኔታ

ይህ ክፍል ስለ መጋዘን ሕንጻ ግንባታና አያያዝ መልካም ተሞክሮዎችን ይገልጻል። የስርጭት ጣቢያ መጋዘን ማለት በአንድ በተመረጠ ቦታ የዕርዳታ ቁሳቁሶች ለተወሰነ ጊዜ ለማከማቸት የሚያገልግል ሕንጻ ማለት ነው። ምግብ ነክ የሆኑ ቁሳቁሶች ለረዥም ጊዜ በስርጭት ጣቢያ መጋዘን ውስጥ መቆየት የለባቸውም።





የእርዳታ ቁሳቁሶች የሚከፋፈሉበትን አስገዳጅ የጊዜ ሰሌዳዎችን በካርድ ቁ. 2 ተመልከቱ::

ይህ ክፍል በሶስት ንዑስ ክፍሎች የተከፋፈለ ነው:-

- ነባር የስርጭት ጣቢያ መጋዘኖች -ነባር መጋዘኖችን ስለ መጠገን እና የመያዝ አቅማቸውን ስለ ማስላት መመሪያዎችን የያዘ ነው።

- ጊዜያዊ ማከማቻ ቦታዎች - የነባሩ መጋዘን የታቀደውን የዕርዳታ ቁሳቁስ የመያዝ አቅም አናሳ በሚሆንበት ወቅት ጊዜያዊ አማራጮችን ያካተተ ሲሆን በተጨማሪም ከመጋዘን ውጪ የዕርዳታ ቁሳቁሶችን በጊዜያዊነት የማቆየት/ የማከማቸት (በመጋዘን የማስቀመጥ ሌሎች አማራጮች ከተሟጠጡ በኋላ የሚወሰድ የመጨረሻ አማራጭ ነው) እንዲሁም ባልታሰበ ድንገተኛ አደጋ ወቅት ከፍተኛ መጠን ያላቸውን የዕርዳታ ቁሳቁሶች የማከማቸት አማራጮች መመሪያን የያዘ ነው።

- የመጋዘን ግንባታ - ወረዳው አዲስ የስርጭት ጣቢያ መጋዘን ለመገንባት በሚወሰንበት ወቅት የስርጭት ጣቢያ መጋዘን ቦታን ስለ መምረጥ እና ደረጃውን የጠበቀ የስርጭት ጣቢያ መጋዘን አንዳንድ ባሕሪያትን ለማጣቀስ መመሪያዎችን ያስቀምጣል።

ነባር የስርጭት ጣቢያ መጋዘኖች

በመልካም ሁኔታና በስርአት ተጠብቆ የሚገኝ መጋዘን ከማማሩ ባሻገር የዕርዳታ ቁሳቁሶችን ከብልሽትና ከመጥፋት ይከላከላል ፡፡ እንደ መጋዘን ሰራተኛነታችሁ ግቢውና መጋዘኑ በመልካም ሁኔታ ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባችሁ፡፡

ያልተፈቀደላቸው ሰዎች እና እንስሳት ወደ ግቢው እንዳይገቡ ለመቆጣጠር አጥርና በሮች ሊኖሩት ይገባል፡-

- የተበላሹትን ክፍሎች መጠገን ወይም በአዲስ መተካት ፣
- የጥበቃ ሰራተኞችን መመደብ ፣
- በቂ ብርሃን እንደሚያገኝ ማረጋገጥ ፣
- ደረጃቸውን የጠበቁ ተንጠልጣይ ቁልፎችን መጠቀም ፣

መንገዶችና የጭነት ማራገፊያ ቦታዎች ለመኪናዎች ደህንነት ምቹ እና እንቅስቃሴያቸውን የማይገድቡ መሆን አለባቸው፡-

- የፍሳሽ ማስወገጃዎች መስራታቸውን ማረጋገጥ ፣
- አባጣ ጎርባጣ መንገዶችን መሙላት ፣
- ጠቋሚ ምልክቶች መኖራቸውን ማረጋገጥ ፣


የመጋዘን ውስጥ መተላለፊያዎች አይጦችን ለመከላከል መጠረግና ንፅህናቸው የተጠበቀ መሆን አለበት፡-

- ቆሻሻዎችን ማስወገድ ፣
- ሳሩን ማጨድ ፣ ቁጥቋጦዎችንና ዛፎችን መመንጠር ፣

ሚዛን ካለ በጥንቃቄ ሊያዝ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ስለ አጠቃቀሙና አጠጋገኑ የተሰጠውን መመሪያ በትክክል መከተል ያስፈልጋል፡፡

በተቻለ ፍጥነት አነስተኛ ጥገናዎችን ማከናወን ይኖርባችኋል፡፡ ከፍተኛ ጥገና የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ፈቃድ በአስቸኳይ መጠየቅ አለባችሁ፡፡

መጋዘን ሕንጻዎች፡- የህንጻዎቹ የውስጥና የውጭ ክፍሎች በመልካም ሁኔታ ሊያዙ ይገባል ፡፡ በወጣው ፕሮግራም መሰረት በዕቅድ ጥገናዎችን ማካሄድ ይመከራል፡፡




የመጋዘን ጣሪያ፡ የሚያንጠባጥቡ ቦታዎችን በመፈለግ መጠገን ወይም ጥገና እንዲካሄድ በአስቸኳይ መጠየቅ፤ ጥገናው አስከሚካሄድ ድረስ የዕርዳታ ምግቡን ውኃ በማያስገባ ፕላስቲክ መሸፈን ፡፡ የላሉ ብሎኖችን ማጥበቅ፣ የተላቀቁ የቤት ክዳን ቆርቆሮዎችን በሚስማር ወይም በብሎን ማጥበቅ::

በሮች፡ ማጠፊያዎችን ወይም ሀዲዶቹን በዘይት ማለስለስ፤ በትክክል እንደሚከፈቱና እንደሚዘጉ ማረጋገጥ፡፡ ቁልፎችና መቀርቀሪያዎች መስራታቸውን ማረጋገጥ፡፡

መስኮቶችና አየር ማስተላለፊያ፡ በትክክል የሚዘጉና የሚከፈቱ መሆን አለባቸው፡ ፡ የተሰበሩ ክፍሎች ካሉ መቀየር ያስፈልጋል፡፡ ከወፎች ለመከላከል የሽቦ ወንፊት መግጠም፡፡

አሸንዳዎችና የፍሳሽ ማስወገጃዎች፡ የዝናብ ወቅት ከመድረሱ በፊት ማጽዳት፡፡ ቦይዎችን ማጽዳት፣ እንደአስፈላጊነቱ መጠገን፡፡



ግድግዳዎች: በተቻለ መጠን የተስተካከለ መሆን አለበት፤ በደንብ በሲሚንቶ ያልተገረፉ ቦታዎችን መጠገን፣ የተሠነጠቁትን መሙላት፣ ግድግዳው ንፅህናው የተጠበቀና የጸዳ መሆን አለበት፡፡

ወለል: የተሰነጠቁ ወለሎችን በኮንክሪት መሙላት፤ ምግብና ቆሻሻዎች በተሰነጠቀው ወለል ውስጥ እንዳይከማቹ በሌሎች ወለል መሙያ ነገሮች መሙላት፡፡

እሳት አደጋ መከላከል: በአደጋ ወቅት በቀላሉ ለመድረስ እንዲያመች በውስጥ በኩል ከበሮቹ በስተጀርባ ማንጠልጠያ ያላቸው የእሳት ማጥፊያዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡ በየጊዜውም እድሳት ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ በመጋዘን ውስጥና በአካባቢው ሲጋራ ማጨስ መከልከል አለበት፡፡

ንፅህና: የዕርዳታ ምግቦች ከመከማቸታቸው በፊት መጋዘኑን ማፅዳት፡፡ ይህንን ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑ የፅዳት እቃዎች ሊኖራችሁ ይገባል፡፡ (ከዚህ በታች የሚገኙትን ተመልከቱ)፡፡

መሰረታዊ የመጋዘን መሳሪያዎች

እያንዳንዱ የስርጭት ጣቢያ መጋዘን የሚከተሉት መሰረታዊ መሳሪያዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡

ሣጥን 1 - የስርጭት ጣቢያ መጋዘን መሰረታዊ መሳሪያዎች

የፅህፈትና የመረጃ አያያዝ መሳሪያዎች :-
- የመዝገብ መደርደሪያዎች
- ጠረጴዛና ወንበር
- የሒሳብ መሳሪያ
- ስቴፕለርና የስቴፕለር ሽቦ
- ወረቀት መብሻ
- ማስመሪያ
- ቦክስ ፋይል
- እስክርቢቶ

የፅዳትና መጋዘን ማዘጋጃ መሳሪያዎች፡-
- መጥረጊያዎች
- መሰላል
- ባልዲ
- የአይጥ ወጥመድ
- አካፋ
- የዕጅ ባትሪ

ቁሳቁሶቹን የመያዣ/የማጓጓዣ መሳሪያዎች፡-

- የእጅ ጋሪ/ ማጓጓዣ ጋሪ
- የፕላስቲክ መሸፈኛ
- የማሸጊያ መሳሪያዎች (ለምሳሌ፥ ወስፌና ክር፣ ባዶ ከረጢቶች፣ ካርቶኖች፣ የምግብ ዘይት መያዣዎች፣ ማጣበቂያ ፕላስተር)
- ናሙና መውሰጃ
- ማበጠሪያ ወንፊት
- ሚዛን

የድንገተኛ አደጋ ጊዜ መሳሪያዎች፡-

- የመጀመሪያ ዕርዳታ መስጫ ሳጥን
- የእሳት ማጥፊያ (የማይገኝ ከሆነ በቂ የሆነ አሸዋ መኖሩን ማረጋገጥ)

የመጋዘን ሰራተኞች መሰረታዊ የሆነ የጥገና ስራዎችን ማካሄድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንን ለማከናወን የሚከተሉት መሳሪያዎች ሊኖራችሁ ይገባል፡-

ሣጥን 2 - የስርጭት ጣቢያ መጋዘን መጠነኛ ጥገና ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ መሳሪያዎች

- ብሎን መፍቻ
- መዶሻ
- መሰርሰሪያ
- የተለያየ መጠን ያለው መፍቻ
- ማጣበቂያ ፕላስተር
- የቀለም ብሩሽ
- ሲሚንቶ
- መሰላል
- ዛቢያ
- ባልዲ
- መጋዝ
- ሜትር

የስርጭት ጣቢያ መጋዘን የመያዝ አቅም ማስላት

የመጋዘኑን የመያዝ አቅም ለማስላት (ወደ እያንዳንዱ ስርጭት ጣቢያ የሚላከውን ከፍተኛ የዕርዳታ ቁሳቁስ መጠን ለመወሰን) የስርጭት ጣቢያ መጋዘኑን ቁመት፣ ርዝመትና ወርድ መለካት አለባችሁ፡፡

ማሳሰቢያ ፥ ቁመቱ የሚለካው በወለሉና በጣሪያው መካከል የሚገኘውን ርቀት በመለካትና ከዚያም አንድ ሜትር በመቀነስ ነው፡፡ (ቁመቱ የተቀነሰበት ምክንያት በቂ አየር እንዲተላለፍ ድርድሩ ጣሪያው ጥግ ድረስ መድረስ ስለሌለበት ነው፡፡)

የመጋዘኑ ቁመት፣ ወርድና ርዝመት በሜትር ከተለካ በኋላ የመያዝ አቅሙን (በኩንታል ወይም በሜትሪክ ቶን) በሚከተለው ዘዴ ማስላት ይቻላል፡-

$$\text{የመያዝ አቅም (በሜትሪክ ቶን)} = \frac{[\text{ወርድ} \times \text{ርዝመት} \times (\text{ቁመት} - 1\text{ሜ})] \times 0.85}{1.8}$$

$$\text{የመያዝ አቅም (በኩንታል)} = \text{የመያዝ አቅም (በሜትሪክ ቶን)} \times 10$$

በድርድሮቹ መካከልና በግድግዳውና በድርድሩ መካከል በቂ ክፍተት እንዲኖር ታስቦ ከስርጭት ጣቢያው መጋዘን የመያዝ አቅም ላይ 15 ፐርሰንት ይቀነሳል (ጠቅላላ አቅሙ በ0.85 ይባዛል)፡፡ በመጨረሻም የሚገኘውን ብዜት/ውጤት በ1.8 በማካፈል የስርጭት ጣቢያውን የመያዝ አቅም በሜትሪክ ቶን ማግኘት ይቻላል፡፡

ምሳሌ፥ ወርድ 50ሜ፣ ርዝመት 100ሜ፣ ቁመት 6ሜ

$$\text{የመያዝ አቅም} = \frac{[50 \times 100 \times (6 - 1) \times 0.85]}{1.8}$$

$$\text{የመያዝ አቅም} = \frac{25{,}000 \times 0.85}{1.8}$$

የመያዝ አቅም = 11,805.5 ሜትሪክ ቶን

የመያዝ አቅም = 11,805.5 ሜትሪክ ቶን x 10 = 118,055 ኩንታል

ከላይ በተቀመጠው ስሌት መሰረት በእናንተ ስር የሚገኙትን የማሰራጫ ጣቢያ መጋዘኖች በሙሉ የመያዝ አቅማቸውን ማስላት ይጠበቅባችኋል፡፡ ስሌቱ የሚያገለግለው ለዕህልና ጥራጥሬ ብቻ ሲሆን ለምግብ ዘይት፣ በካርቶን ለታሸጉና ጣሳዎች አያገለግልም፡፡ ለካርቶኖችና ጣሳዎች የመያዝ አቅም የሚወሰነው በመያዣዎቹ ስፋትና ቅርፅ መሰረት ይሆናል፡፡

ጊዜያዊ ማከማቻ ቦታዎች

የስርጭት ጣቢያ መጋዘኖች በማይኖሩበት አካባቢ ወይም መጋዘኑ የታቀደውን የዕርዳታ ቁሳቁስ የመያዝ አቅም ባይኖረው ወረዳው የሚከተሉትን አማራጮች መፈለግ ይኖርበታል፦

- የመንግስት ሕንፃዎችን/የማህበረሰብ ተቋሟትን መጠቀም (ለምሳሌ፥ የስብሰባ አዳራሾችን ወይም የሚመለከተውን ኮሚቴ በማስፈቀድ ትምህርት ቤቶችን መጠቀም)፣
- አስቀድሞ በመስማማት የስርጭት ጣቢያ መጋዘኖችን መከራየት፣

ከላይ የተጠቀሱት አማራጮች የማይገኙ ከሆነ አስቸኳይ ጊዜያዊ መጋዘኖችን መጠቀም::

እንደ መጨረሻ አማራጭ (ለምሳሌ፥ ባልታሰበ ድንገተኛ አደጋ ወቅት ከፍተኛ መጠን ያላቸው የእርዳታ ቁሳቁሶች ለማከማቸት አስቸኳይ ጊዜያዊ ማከማቻ ቦታዎች የማይገኙ ከሆነ) የሚከተሉት ነገሮች መሟላት የሚችሉ ከሆነ ብቻ ከመጋዘን ውጭ የዕርዳታ ቁሳቁስን ደርድሮ ማስቀመጥ ይቻላል፥-

- የዕርዳታ ቁሳቁሱን ሙሉ በሙሉ ለመሸፈን በቂ የፕላስቲክ መሸፈኛ ከተገኘ፣
- የበጋ ወቅት ከሆነ እና ዝናብ የማይዘንብ ከሆነ፣
- የዕርዳታ ቁሳቁሶቹን በአጭር ቀናት ውስጥ ለማከፋፈል የሚቻል ከሆነ፣
- የሚመለከተው ኃላፊ ከፈቀደ፥፥


አስቸኳይ ጊዜያዊ ማከማቻ ቦታ

ተገጣጣሚ የስርጭት ጣቢያ መጋዘን


በአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ወቅት መደበኛው የስርጭት ጣቢያ መጋዘን ከሚይዘው በላይ የዕርዳታ ምግብ መያዝ አስፈላጊ ነው፥፥ አንዳንዶቹን ከታች በተቀመጠው መሰረት ውጭ መደርደር ይቻላል ነገር ግን በቀላሉ ለመገጣጠምና እንደአስፈላጊነቱ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ተገጣጣሚ መጋዘኖችን መጠቀም ይመረጣል፥፥

እነዚህ መጋዘኖች ለአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ታስበው የተዘጋጁ ቢሆኑም በቂ አየር

ማስገቢያ ካልኖራቸው ግን በጣም ሊሞቁ ይችላሉ፡፡ ይህ እንዳይሆን በስተጀርባ ያሉትን በሮች በመክፈት ወይም በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ፋኖችን በመግጠም የአየር ዝውውሩን ማሻሻል ይቻላል፡፡ መሬት ላይ የሚፈሰውን ውሃ ወደ መጋዘን እንዳይገባ ለመከላከል የፍሳሽ ማስወገጃ ቦዮች ያስፈልጋሉ፡፡ የመጋዘኑ ወለል ከሲሚንቶ ካልተሰራ ወይም እርጥበት እንዳያሳልፍ ካልተደረገ እንዲሁም በጣሪያው ውስጥ የሚንጠባጠብ ውሃ ካለ ምግቡን ሊያበላሽ ይችላል፡፡ ስለዚህም ከመደበኛ የስርቄት ጣቢያ መጋዘን የበለጠ አይጦችና ምስጦችን ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህም ባሻገር የመደርደሪያዎች መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ በተደጋጋሚ ምርመራ ማካሄድም ያስፈልጋል፡፡



የመርብ ኮንቴነሮችን መጠቀም



ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን የዕርዳታ ቁሳቁሶች ለማስቀመጥ የመርከብ ኮንቴነሮች አስተማማኝ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፦ የምግብ ዘይት በቂ ከለላ ካላገኘ በቀላሉ ሊሞቅ ይችላል፡፡ ብዛት ካለው በቀላሉ መደርደር ይቻላል፡፡

ከመጋዘን ውጭ ደርድሮ ማስቀመጥ

የስርጭት ጣቢያ መጋዘን የመያዝ አቅሙ በሚያንስበት ወቅት የተወሰኑትን ዕርዳታዎች ከመጋዘን ውጭ ማኖር አስፈላጊ ነው ፡፡ በውጭ ማቆየት የሚቻለው ዕህል ፣ ጥራጥሬና የምግብ ዘይት ሲሆኑ ዱቄቶች ፣ ቅይጥ ምግቦች ፣ የዱቄት ወተት ወይም የጣሳ ምግቦች ግን ከመጋዘን ውጭ መቆየት የለባቸውም ፡፡

በውጭ ማከማቸት ውጤታማ እንዲሆን የሚከተሉት ነገሮች ያስፈልጉታል ፡-

- ተስማሚ ስፍራ ፣
- የተዘጋጀ የመደርደሪያ ስፍራ ፣
- ከስር የሚደረግ መደርደሪያና ዝናብ የማይገባበት መሬት ላይ የሚነጠፍ ፕላስቲክ ፣
- ውሀ የማያስገባ ሽራ (መሸፈኛ) ፣
- ሽራ ማሰሪያ ገመድ

የሚገኝበት ቦታ


የሚገኝበት ቦታ የሚከተለውን መምሰል አለበት ፡-

- አስተማማኝ ጥበቃ ያለውና በአጥር ወይም በግድግዳ የተከለለ ፣
- ለጭነት መኪኖች ምቹ የሆነ ፣
- ጥብቅ ፣ ሚዳማና ለፍሳሽ ማስወገጃ ተዳፋትነት ያለው ፣
- ለጎርፍ ያልተጋለጠ ፡፡

ከፍታ ስፍራ


ድርድሩ ከመሬቱ ውሀ ልክ ከፍ ብሎ መገንባት አለበት ፡፡ በጊዜያዊነት ለመጠቀም መሰረቱን ከመሬት ከ0.3 ሜትር እስከ 0.6 ሜትር ከፍታ በአፈር መጠቅጠቅ ያስፈልጋል ፡፡ እርጥበታማ የሆነውን ከፍታ ስፍራ ለመስራት ጠጠሮችን መጠቀም ፡፡ ከላይ ያለውን ልል አፈር በማንሳት እስከ 0.3 ሜትር በሚደርስ ከፍታ ትላልቅ ድንጋዮችን

ከመሰረቱ ስር እንዲሁም ትናንሽ ድንጋዮችን ከላይ በማድረግ መጠቅጠቅ፡፡ በአፈርና በጠጠር የተሰራው ከፍታ ዙሪያ የፍሳሽ ማስወገጃ ቦይ በመቆፈር ወደ ድርድሩ የሚገባ ውሀ በቀላሉ እንዲወገድ ማድረግ፡፡ የብሎኬት ጎርፍ መከላከያ ያለው፣ ፅኑ መሰረት የሆነ በተመረጠ አፈር የተጠቀጠቀ እና የከፍታውን ወለል በብሎኬት ወይም በአስፋልት በመገንባት ቋሚ የሆነ ከፍታ መገንባት ይቻላል፡፡



መደርደሪያና የመሬት ንጣፍ

የቁሳቁሱን ድርድር ለመሰራት መደርደሪያዎች ወይም ባለሁለት ረድፍ ተደራራቢ አጠና ያስፈልጋል፡፡



ከፕላስቲክ የተሰራ የመሬት ንጣፍ ከመጀመሪያው ዙር የከረጢት ድርድር አናት ላይ መነጠፍ አለበት፡፡ ከዚያም የድርድሩን መሰረት ከመሸፈን ባሻገር በሶስተኛና በአራተኛ ዙር ድርድር መሀል ያሉትን ጥጋጥጎች ፕላስቲኩን በመሸንጥ ከጎርፍ መከላከል ይገባል፡፡

መሸፈኛዎች

ውሃ የማያሳልፍ መሸፈኛ ከሸራ ወይም ከፕላስቲክ ሊሰራ ይችላል፡፡ ድርድሩ በቂ አየር በማግኘት እንዲናፈስ እና በሙቀት ጊዜ ወበቅ ወይም ላቦት እንዳይፈጠር ስለሚረዳ የሸራ መሸፈኛ ከፕላስቲክ መሸፈኛ ይመረጣል፡፡ መሸፈኛው በደንብ አድርጎ ለመሸፈን እንዲያመች በቂ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም በገመድ ለማሰር እንዲያመች ለዚሁ አላማ የተበሱ ቀዳዳዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡ የታሰረውን ሸራ/ ፕላስቲክ የድርድሩን አናት፣ ጎን እና የታችኛውን ክፍሎች ለመሸፈን በቂ የሆነ ፕላስቲክ በተጨማሪም


ፕላስቲኮቹ የሚገጣጠሙበት ቦታ በበቂ ሁኔታ ተደራራቢ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ፕላስቲኮች ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት የፕላስቲኮቹን ጥንካሬ ማረጋገጥ ካስፈለገም በቶሎ መጠገን መልካም ነው፡፡

ገመዶች

ቀጠን ያለ ገመድ መሸፈኛውን አጥብቆ ለማሰር ይጠቅማል፡፡ ገመዱ ከድርድሩ ጋር ከታሰረ በኋላ መሬት ላይ ካለው ችካል ጋር ማሰር ወይም ክብደት ባላቸው አሮጌ ጎማዎች ላይ ማሰር ይገባል፡፡

ድርድር

የስርጭት ጣቢያ መጋዘን ድርድር ለመስራት ተመሳሳይ መመሪያ መጠቀም፡፡




ምናልባት ለቆጠራ ቢያስቸግርም ድርድሩ ጥብቅ እንዲሆን ወደ መሀል ያጋደለ መሆን አለበት፡፡ ወደ ላይ ተቀስቶ የሚሰራ ጣሪያ የዝናብ ውሃ ድርድሩን ሳይነካ እንዲፈስ ይረዳል በተለይ ውጭ ለሚሰራ ድርድር ጠቃሚ ነው፡፡

አሸፋፈን

ብዙ ጊዜ የዝናብ መከላከያ ላስቲክ የድርድሩን ጎኖች በሙሉ እና አናቱን ለመሸፈን በቂ አይሆኑም፡፡ በዚህ ጊዜ የሚከተሉትን ዘዴዎች መጠቀም መልካም ነው፡-


- በአንድ ጎን የሚገኘውን መሸፈኛ የታችኛውን ክፍል ለመሸፈን መጠቀም ፣
- ላስቲኩን በደንብ በመወጠርና በገመድ ወይም በድርድሮቹ መሀል በመሸጎጥ መሸፈን ፣

- በጎን የሚገኙትን ላስቲኮች ረዘም በማድረግ አናቱን መሸፈን፣
- አናቱ የተሸፈነበት የፕላስቲክ ጫፍ ከድርድሩ ወይም ከችካሉ ጋር ማሰር፣




የዝናብ መከላከያ ላስቲኮችን ለመገጣጠም የሚከተሉትን ዘዴዎች መጠቀም ይቻላል፡-

1. ከንፋስ አቅጣጫ በተቃራኒ አንድ ሜትር የሚያህል ላስቲኮቹ የሚገጣጠሙበትን ቦታ መደራረብ



2. የአስተዳደር ስርዓት



አስተዳደር

ድርድሮች በየቀኑ ሊፈተሹ ይገባል፡፡ የሚከተሉት ችግሮች አለመፈጠራቸውን ማጣራት ያስፈልጋል፡-

- ወደ ድርድሩ ዘልቆ የገባ ውኃ አለመኖሩን፣
- የተበጠሰ ወይም የላላ ገመድ አለመኖሩን፣
- የተደፈነ ፍሳሽ ማስወገጃ አለመኖሩን፣

ፀሐያማ በሆኑ ቀናት የድርድሩን አናት ላስቲክ በመፍታት በድርድሩ ላይ የተከማቸ እርጥበት ካለ እንዲተን ማድረግ::

የመጋዘን ግንባታ

ለመጋዘን ግንባታ ቦታ መምረጥ

የስርጭት ጣቢያ መጋዘን በሚከተሉት መስፈርት መሰረት በጥንቃቄ መመረጥ አለበት፡-


- ለትራንስፖርት ምቹ የሆነ፣
- ከከተማ ወይም ከመንደር ወጣ ያለ እና የተጨናነቀ ስፍራ ሳይሆን በቂ አየር የሚገኝበት፣
- ደህንነቱን ለማረጋገጥ ለውጭ ጥቃቶች ያልተጋለጠ (የራሱ አጥርና ጥበቃ ያለው) ፣
- የመጋዘኑ አካባቢ ከአረም ፣ ከቁጥቋጦና መሰል ተክሎች የጸዳ ፣
- ለጎርፍና ለእሳት አደጋ ያልተጋለጠ፡፡

ደረጃውን የጠበቀ የስርጭት ጣቢያ መጋዘን መስፈርቶች

ምግብ ነክ ቁሳቁሶችን ለማስቀመጥ መጋዘኖች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው:-

- ግድግዳዎች ፣ ጣሪያው ፣ መስኮቶችና በሮች ዝናብ የማያስገቡ መሆን አለባቸው ፣
- ወፎችንና አይጦችን ማስገባት የሚችሉ ቀዳዳዎች መኖር የለባቸውም ፣
- የመጋዘኑ ወለል በተቻለ መጠን ለስላሳና 10 ሳ.ሜትር ውፍረት ባለው ሲሚንቶ የተሰራ መሆን አለበት ፣
- በሮቹ ጠንካራና በቀላሉ የሚከፈቱና የሚዘጉ መሆን አለባቸው ፣
- ወደ ውስጥ እና ከግድግዳው አናት ላይ የሚገኙት መስኮቶች አየር ማስተላለፍ እንዲችሉ የሽቦ ወንፊት ሊገጠምላቸው ይገባል ፣
- በስርጭት ጣቢያው መጋዘን ዙሪያ የዝናብ ውሀና ጎርፍ ማስወገጃ ቦይ መቆፈር አለበት ፣
- መጋዘኑ በቂ የፀሀይ ብርሀን የሚያገኝ መሆን አለበት ፣
- የስርጭት ጣቢያ መጋዘን ዙሪያ ከአረሞችና ቁጥቋጦዎች ነፃ መሆን አለበት ፣
- ንጽህናውን ሁልጊዜ መጠበቅ ፣
- አካባቢውን ከማንኛውም አይነት የእሳት አደጋ ነፃ መሆን አለበት::

8



የቃላት ትርጉም

8 የቃላት ትርጉም

ቃላት	ትርጉም/ማብራሪያ
ተጠቃሚዎች	ከልማታዊ ሴፍቲኔት ወይም ከዕርዳታ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሚሆነው ሕዝብ ማለትም በቀጥታ ዕርዳታው የሚደርሳቸው ሰዎች ማለት ነው ፡፡
የተጠቃሚነት መብት	በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በመሳተፋቸው (በማህበረሰብ የልማት ሥራ ወይም በቀጥታ ድጋፍ የተመዘገቡ) ወይም በተረጅነት በመመዝገባቸው እንዲያገኙ የሚገባቸው የዕርዳታ መጠን ማለት ነው ፡፡
ያለተጨማሪ መሰፈርት ማሰራጨት	ተጨማሪ የልየታ (targeting) መሰፈርት ሳያስፈልግ በአንድ በተመረጠ አካባቢ ወይም ማህበረሰብ የሚገኘውን ሁሉንም ሰው የሚያካትት የዕርዳታ ስርጭት ማለት ነው ፡፡
ግልባጭ	በእጅ የተጻፈ ወይም የተተየበ ዕሁፍ ቅጅ (የካርቦን ግልባጭ)
በኮምፒውተር የታገዘ የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች ድልድልና ክትትል ሥርዓት (CATS)	በአደጋ መከላከል ዝግጁነት እና ምግብ ዋስትና ዘርፍ ተልከው በክልል መንግስታት በኩል የሚሰራጩትን የዕርዳታ ቁሳቁስ በኮምፒውተር በታገዘ ዕቅድ ፣ ድልድልና ክትትል ሥርዓት በፌዴራልና በክልል ደረጃ በመጠቀም መሰራት ፡፡
ተሳታፊ/ተጠቃሚ/ደንበኛ	የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎችን የሚያመለክት ስያሜ ነው ፡፡
የተሳታፊ/ ተጠቃሚ ክፍያ	ለተሳታፊ የሚከፈል ተብሎ ይታወቃል ፡፡ በአብዛኛው የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች በአካባቢያቸው በሚደረግ የልማት ሥራ በመሳተፋቸው በገንዘብ ወይም በአይነት/ ዕርዳታ ቁሳቁስ የሚከፈላቸው ክፍያ ማለት ነው ፡፡
ምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ ዕርዳታ	ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የዕርዳታ አይነት ሲሆን ለምሳሌ ከመሰረታዊ ምግቦች (እንደ ጥራጥሬ ፣ የተለያዩ ሰብሎች ፣ የምግብ ዘይት) እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ነገር ግን ከሌሎች ተመሳሳይ ቁሳቁሶች ጋር ሊቀያየሩ የሚችሉ ናቸው ፡፡ በሴፍቲኔትና በዕርዳታ ፕሮግራሞች አግባብ መሰረት ለተጠቃሚዎች የሚከፋፈል ማንኛውም መሰረታዊ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ይጨምራል ፡፡
ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የዕርዳታ ቁሳቁስ መጥፋት	ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታ ቁሳቁሶች ብዛት መቀነስ ማለት ነው ፡፡

ቃላት	ትርጉም/ማብራሪያ
ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የዕርዳታ ቁሳቁስ መጥፋት	ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች ከሚጠበቀው ለምግብነት መዋል ይዘት ደረጃ መቀነስ፡፡ ለምግብ ነክ ቁሳቁሶች ተመጣጣኝ ንጥረ ነገር፣ የመልክና የጥራት መቀነስ/ መለወጥ ማለት ነው፡፡ ደረጃዉን የማያሟላ ምግብ በተጠቃሚው ማህበረሰብ ላይ ሰፊ ጉዳት ያስከትላል፡፡ የተበላሹ ምግቦች መገለጫቸው የሚከተሉት ናቸው፡- - የመልክ መቀየር፣ - ያልተለመደ ሽታ ወይም ግማት፣ - መሻገት፣ - የክብደት መቅለል፣ - የምግብ ይዘት ደረጃ መቀነስ፣ - የመብቀል ዕድል ማነስ፣
ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎችን ከታለመለት ዓላማ ውጪ ማዋል	ከልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ወይም ከዕለት ዕርዳታ አሰራር ውጪ ለሌላ አላማ ሲውል የተወሰኑ የዕርዳታ ቁሳቁስ አይነቶች ይጠፋሉ፡፡ ይህም የሚከሰተው በስርቆት ወይም በስርጭት ላልተካተቱ የህብረተሰብ ክፍሎች ዕርዳታው ሲታደል ነው፡፡
ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች አስተዳደር	ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የዕርዳታ ቁሳቁስ ስርቆትን ወይም ብልሽትን ለመቀነስ በተጠቃሚው ግለሠብ ወይም ማህበረሰብ ወይም ድርጅት በቀጥታ ቁጥጥር ስር የሚገኝበትን ሰፍራ፣ሁኔታ እና መጠን የመከታተልና የመመዝገብ አሰራር ነው፡፡
ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎችን ማጓጓዝ	ከአንድ ሰፍራ ወደሌላ ሰፍራ የሚደረግ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የዕርዳታ ዝውውር ሲደረግና አንዳንዴ ንብረቱ ከሰፍራው ሳይንቀሳቀስ የባለቤትነት ለውጥ ስለመደረጉ የሚያመለክት መግለጫ ነው፡፡
አደጋ	በተፈጥሮ እና በሰው ሰራሽ አደጋ ምክንያት በተወሰነ አካባቢ ላይ ተፅዕኖ ሲያሳድር (በተጋላጭ ማሕበረሰብ፣ በአንድ አካባቢ እና በተመረጠ መሠረተ ልማት ላይ ወይም በርካታ ሕዝብ ተፈናቅሎ በአንድ አካባቢ ሲጠለል) በንብረትና በሰው ላይ ጥፋት ሲደርስ፣ የተጎዳው ማህበረሰብ የዕለት ተግባሩን ማከናወን ሲሳነው፣ ችግርን የመቋቋም አቅማቸው ሲመናመን እና ለመኖር የሌሎችን ድጋፍ ሲፈልጉ የሚፈጠር ክስተት ነው፡፡
ዕርዳታ መላክ	ወደ አንድ ሰፍራ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎችን መላክ ነው፡፡ በሴፍቲኔት እና በዕለት ዕርዳታ ፕሮግራሞች አግባብ ከአደጋ መከላከል ዝግጁነት እና ምግብ ዋስትና ዘርፍ ማዕከላዊ መጋዘኖች ወደ ስርጭት ጣቢያዎች የዕርዳታ ቁሳቁስ በጭነት መኪና ማጓጓዝ ነው፡፡

ቃላት	ትርጉም/ማብራሪያ
የስርጭት ኮሚቴ	ማህበረሰቡን ወክለው የእርዳታ ቁሳቁስ ስርጭትን እንዲቆጣጠሩ በወረዳው የተቋቋሙ አካላት ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ቀበሌ አንድ የስርጭት ኮሚቴ መቋቋም ይኖርበታል፡፡ የስርጭት ኮሚቴ የተውጣጡት ከግብረ-ኃይል በተለየ መልኩ ከማህበረሰብ አካላት ነው (ልየታን እና የአልሚ ምግብ ስርጭትን ከሚቆጣጠረው ከጤና ኤክስትንሽን ሰራተኛ በስተቀር)፡፡
ፈጣን ምላሽ	በአደጋ ጊዜ ሕይወትን ለማዳንና የማህበረሰቡን መተዳደሪያ ጠብቆ ለማቆየት የሚሰጥ መሰረታዊ የቁሳቁስና አገልግሎቶች ድጋፍ ነው፡፡
ያልታሰበ ድንገተኛ አደጋ	ያለምንም ወይም በመጠነኛ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ (ሳይታሰብ ወይም ዝግጅት ሳይደረግ) የሚከሰት አደጋ ሲሆን በሰዎች ሕይወት፣ ኑሮ እና በዕለት ተዕለት ተግባር ላይ ቅፅበታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥር ሁኔታ ነው፡፡ በተፈጥሮ አደጋ ከሚጠቀሱት ውስጥ ጎርፍ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ናዳና አውሎንፋስ ሲሆኑ በሰው ሰራሽ ደግሞ ግጭቶችና አስገድዶ ማፈናቀል የመሳሰሉት ናቸው፡፡
የስርጭት ጣቢያ	የዕርዳታ ዕህል ስርጭት ጣቢያ ማለት ነው፡፡ በየእርዳታ ቁሳቁሶቹ ወደ ተጠቃሚዎች የሚተላለፉበት ስፍራ ነው፡፡ ቋሚ የስርጭት ጣቢያ ማለት ለክምችት አገልግሎት የተገነባ ሕንፃ/መጋዘን ወይም በቀጣይነት የመጋዘን አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ (ምናልባት ወረዳው ያስገነባው፣ የተከራየው ወይም የተዋሰው) ሊሆን ይችላል:: የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ/ፕሮግራም እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ ዕርዳታውን ለማከፋፈል ምቹ ቦታ እንደሆነ ቀደም ሲል በዕቅድ የተያዘ መሆን አለበት፡፡
መደበኛ ምግብ ስርጭት	መሰረታዊ የተመጣጠነ ምግብ ደረጃን የሚያሟሉ ኃይል ሠጪና ፕሮቲን ምግቦችን በመደበኛ ሁኔታ ማከፋፈል፡፡
የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ	ቁሳዊ ጥፋት ሊያስከትል የሚችል፣ በሕይወትና በንብረት ላይ ጥፋትና ጉዳት ሊያደርስ የሚችል፣ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ወይም የአካባቢ ጥበቃ ላይ ጉዳት

ቃላት	ትርጉም/ማብራሪያ
የቀበሌ ግብረ-ኃይል	ከተለያዩ ክፍሎችና መስሪያ ቤቶች በተውጣጡ ሰዎች በቀበሌ ደረጃ የተዋቀረ ኮሚቴ ሲሆን ተጠቃሚዎችን በመለየት፣ የዕለት ዕርዳታንና የሴፍቲኔት ፕሮግራሞችን የምግብ ድጋፍ በኃላፊነት የሚመሩ ናቸው፡፡ ፡ በዚህ አነስተኛ የመጋዘን ሰራተኞች መመሪያ ውስጥ በተደጋጋሚ የቀበሌ ግብረ-ኃይል ተብሎ የተጠቀሰው የሚያመላክተው በሴፍቲኔት ወረዳዎች፣ ጊዜያዊና ቋሚ የዕለት ዕርዳታ በሚሰጥባቸው በሴፍቲኔት ባልታቀፉ ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙትን የቀበሌ የምግብ ዋስትና ግብረ-ኃይሎችን ነው፡፡
ክትትልና ግምገማ ክትትል	ቀጣይነት ያለው ስራ ሲሆን በተወሰኑ ጠቋሚዎች መሰረት በቋሚነት መረጃ በመሰብሰብ ውጤታማነታቸውን በተመለከተ ለስራ ሐላፊዎች መረጃ ይሰጣል፡፡ በሌላ በኩል ግምገማ ደግሞ የተሰበሰቡት መረጃዎች በመፈተሽ የእርዳታ ቁሳቁስ አስተዳደር ሥርዓቱን ቀልጣፋነት፣ ውጤታማነትና ዘላቂነት ያረጋግጣል፡፡
አስቀድሞ በማጓጓዝ ማከማቸት	በቅድሚያ የተተነበየ አደጋን ለመድረስ ስትራቴጂካዊ በሆኑ ቦታዎች ላይ የዕርዳታ ቁሳቁሶችን አስቀድሞ በማከማቸት ችግሩ ሲከሰት ተደራሽነትን ማረጋገጥ ፤ ለምሳሌ አንዳንድ አካባቢዎች በክረምት ወራት ስለማይደረሱ አስቀድሞ ማከማቸት ያስፈልጋል ፤ ክምችቱ በማራገፊያ ጣቢያዎች ወይም በአማካይ መጋዘኖች ሊሆን ይችላል፡፡ የቅድሚያ መጠባበቂያ ክምችት የሚፈጀውን ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለብዙ ጊዜ ለሚከማች ዕርዳታ የረዥም ጊዜ የመጋዘን አከመቻቸት ተሞክሮዎችን መጠቀም ይገባል፡፡
ልማታዊ ሴፍቲኔትፕሮግራም	ይህ የመንግስት ፕሮግራም ሲሆን በማህበረሰብ የልማት ስራዎች ለተሳተፉ ሰዎች የሚከፈልገንዘብ ወይም የሚሠጥ ምግብ ነው፡፡ (በልማት ለመሳተፍ አቅም ለሌላቸው በቀጥታ ድጋፍ ይደረግላቸዋል)፡፡
የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ቀበሌ	በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የትግበራ ማንዋል ትርጉም መሠረት ስር በሰደደ የምግብ እጥረት የሚታወቅ ቀበሌ ማለት ነው፡፡
የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ወረዳ	በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የትግበራ ማንዋል ትርጉም መሠረት ስር በሰደደ የምግብ እጥረት የሚታወቅ ወረዳ ነው፡፡
የዕለት ዕርዳታ	ሕይወትን ለማዳንና ጉዳትን ለመቀነስ ታስቦ የሚደረግ ዕርዳታ ነው፡፡ እንዲሁም አደጋ ከተከሰተ በኋላ ወዲያውኑ የሚወሰዱ ሕይወት የማዳን፣ ኑሮን የመደገፍ ተግባራት እና መሰረታዊ ሠብዓዊ ፍላጎቶችን የማሟላት ሥራዎችና አስፈላጊ አገልግሎቶችን በጊዜያዊነት እንደቀድሞ ማስጀመር የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ቃላት	ትርጉም/ማብራሪያ
አልሚ ምግብ ስርጭት	ለተጨማሪ የተመጣጠነ የምግብ ስርጭት ከፍተኛ ፍላጎት ለሚታይባቸው ለምሳሌ ነፍሰጡሮች፣ ለሚያጠቡ እናቶችና ሕጻናት) እና ሌሎች በተመጣጠነ ምግብ እጥረት በተወሰነ ደረጃ ለተጎዱ ተጨማሪ አልሚ ምግብ ማሰራጨት ነው። ይህ የተመጣጠነ የምግብ ስርጭት የተሻለ ጠቀሜታ እንዲኖረው ዋናውን የምግብ ስርጭት በበቂ ሁኔታ እያገኙ እንደሆነ መረጋገጥ አለበት።
ልየታ (targeting)	የምግብ እጥረት ያለባቸውን ቤተሰቦች በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ወይም በዕለት ዕርዳታ ፕሮግራም እንዲታቀፉየመለየት ሒደት ነው።
የወረዳ ግብረ-ኃይል	ከተለያዩ ክፍሎችና መ/ቤቶች የተውጣጣ በወረዳ ደረጃ የተዋቀረ ኮሚቴ ሲሆን ተጠቃሚዎችን በመለየት፣ የዕለት ዕርዳታንና የሴፍቲኔት ፕሮግራሞችን ምግብ ድጋፍ በኃላፊነት የሚመራ። በሴፍቲኔት ወረዳዎች እንዲሁም ጊዜያዊና ቋሚ የዕለት ዕርዳታ በሚሰጥባቸው በሴፍቲኔት ያልታቀፉ ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙ የወረዳ የምግብ ዋስትና ግብረ-ኃይሎች የሚመለከት ነው።

ምሕፃረ-ቃላት

ምሕፃረ-ቃል	ፍቺ
አ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ	የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እና የምግብ ዋስትና ዘርፍ
መ.ያ.ድ	መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት
አ.መ.ል.ድ	አማራ መልሶ ማቋቋም ልማት ድርጅት
እ.አ.አ	እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር
እ.ኢ.አ	እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር
RO	የእርዳታ ቁሳቁስ መልቀቂያ ሰነድ
WPR	የእርዳታ ቁሳቁስ መጠየቂያ ሰነድ
SNNPR	የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዘቦች ክልላዊ መንግስት
WFP	የዓለም ምግብ ፕሮግራም
FDP	የስርጭት ጣቢያ
PSNP	የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም

ማጣቀሻ

ርዕስ	ፀሐፊ	ቀን
ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች አስተዳደር ማንዋል	የኢ/ፊ/ዲ/ሪ በግብርና ሚ/ር የአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ	ህዳር 2014 አአአ
ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች መመሪያ	አማራ መልሶ ማቋቋም ልማት ድርጅት	ጥቅምት 2005 አአአ
የመጋዘን አስተዳደር፣ ለመጋዘን ሰራተኛ የዕርዳታ ምግብ አያያዝ መመሪያ	የአለም ምግብ ድርጅት	2001 አአአ


1
2
3
4
5
6
7
8

አስገዳጅ ቅፆችና ፎርሞች

የኢትዮጵያ መንግስት በስርጭት ጣቢያ ደረጃ ለሚገኙ የመጋዘን ሰራተኞች እንዲጠቀሙባቸው የሚከተሉትን ዋና ዋና የዕርዳታ ቁሳቁስ አስተዳደር ሠነዶችን አጽድቋል፡፡

1. የመረከቢያ ሠነድ

በክልሉ መንግስት የሚሰጥ ግልባጭ ያለው ፓድ/ዋራዝ ሲሆን፤ በሙ በየክልሉ ሊለያይ ይችላል፡፡

እንደ መጋዘን ሰራተኛነታችሁ የተወሰነ መጠን ያለውን የዕርዳታ ቁሳቁስ የመጠበቅ ኃላፊነትን ከአሽከርካሪው ወደ እናንተ ለማስተላለፍ የሚያገለግል ሠነድ ነው፡፡ በመረከቢያ ሰነድ ውስጥ በተቀመጠው ዝርዝር መሰረት የመረከቢያ ሰነድ በመቁረጥ የእርዳታ ቁሳቁሱን አይነትና መጠን በይፋ መረከባችሁን መግለጫ ነው፡፡ ከዕርዳታ ቁሳቁሶቹ ጋር ተያይዞ የመጣውን የአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የወጪ ሰነድ ቁጥር በመመዝገብና የተረከባችሁትን ቁሳቁሶች ብዛትና ሁኔታ ከማዕከላዊ መጋዘን ወደ ስርጭት ጣቢያ በሚጓዝበት ወቅት የጠፋ ወይም የተጎዱ/የተበላሹ ቁምር መመዝገብና መግለጽ ይኖርባችኋል፡፡

2. የስርጭት ጣቢያ የወጪ ሠነድ

በክልሉ መንግስት የሚሰጥ ግልባጭ ያለው ፓድ/ዋራዝ ፤ሰሙ በየክልሉ ሊለያይ ይችላል፡፡

በወጪ ትዕዛዝ እና/ወይም በመጠየቂያ ሠነድ ላይ ወረዳው ባፀደቀው መመሪያ መሰረት ለማሰራጨት ሥልጣን የተሰጠው አካል (ለምሳሌ፥ የቀበሌ ሊ/መንበር) ዕርዳታውን እንዲያከፋፍል የሚሰጥ ሠነድ ነው፡፡ ለማሰራጨት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማሰራጫ ጣቢያ የወጪ ሰነድ በመሰጠት የተጠቀሱትን የእርዳታ ቁሳቁሶች አይነትና ብዛት በይፋ ማስተላለፋችሁን ያረጋግጣል፡፡

3. የስርጭት ጣቢያ ሌጀር/መዝገብ

በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰራበት ሌጀር/ መዝገብ ነው፡፡

በስርጭት ጣቢያ የሚገኘውን የክምችት ሁኔታ አጠቃላይ ግንዛቤ የሚሰጥ ሲሆን ጣቢያው የተረከበውን፣ ወጪ ያደረገዉን እና ከወጪ ቀሪ ያለውን የሚያሳይ ሲሆን በተጨማሪም በመጋዘን ውስጥ የጠፋትን ያጠቃልላል፡፡

4. የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የገቢ ሪፖርት

አገር አቀፍ ግልባጭ ያለዉ ዋራዝ

የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የገቢ ሪፖርት (በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰራበት ግልባጭ ያለው ፓድ/ዋራዝ ነው)፡- በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር መሰረት ወር በገባ በመጀመሪው ቀን ወርሃዊ ሪፖርቱ ተጠናቅቆ ለወረዳው መላክ አለበት፡፡ በስርጭት ጣቢያ የተራገፈው መጠን ከማዕከላዊ መጋዘን ከተላከው ጋር ለማመሳከር ይጠቅማል፡፡ ሪፖርቱ የሚያካትተው ባለፈው ወር ወደ ስርጭት ጣቢያው የገባውን የዕርዳታ መጠን፣ ከአ/መ/ዝ/መ/ዋ/ዘ ማዕከላዊ መጋዘን ዕርዳታው ሲላክ ወጪ የተደረገበት ሠነድ ቁጥር እና በስርጭት ጣቢያው ሲራገፍ ገቢ የተደረገበት ሠነድ ቁጥር ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከስርጭት ጣቢያ የተከፋፈሉ እና ገቢ የተደረጉ እንዲሁም በጉዞ ወቅት የጠፋትን ይጨምራል፡፡

5. የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የክምችት ሁኔታ ሪፖርት

በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰራበት ግልባጭ ያለው ፓድ/ዋራዝ::

ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን ወርሃዊ ሪፖርቱን አጠናቃችሁ ወደ ወረዳው መላክ አለባችሁ፡፡ አጠቃላይ ገቢ የተደረገ የዕርዳታ መጠን፣ በቀደመው ወር ከስርጭት ጣቢያ የተከፋፈለና የወሩ መጀመሪያ ከወጪ ቀሪ፣ በመጋዘን የተበላሸ እና የወሩ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ በአጠቃላይ በስርጭት ጣቢያ መጋዘን ገቢና ወጪ የተደረጉትን የሚያሳይ ነው፡፡

መዝገብ አያያዝ

የሚከተሉት መረጃዎች በተቀላጠፈና በቀላሉ የሚገኙበት ቦታ መቀመጣቸውን ማረጋገጥ የእናንተ የመጋዘን ሰራተኞች ኃላፊነት ነው፡፡

የአሰራር ቅደም ተከተል	መረጃ/መዝገብ	ቋሚ የስርጭት ጣቢያ	የወረዳው ጽ/ቤት
የእርዳታ ቁሳቁሶችን መረከብ	የአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ ወጪ ሠነድ + የመረከቢያ ሠነድ		✓ በመረከቢያ ሠነድ ጥራዝ ላይ
	የስርጭት ጣቢያ መጋዘን መዝገብ/ሌጀር	✓	
የእርዳታ ቁሳቁሶችን ወጪ ማድረግ	የዕቃ መጠየቂያ ሠነድ* + የመልቀቂያ ትዕዛዝ* + የስርጭት ጣቢያ ወጪ ሰነድ		✓ በስርጭት ጣቢያ የወጪ ሰነድ ጥራዝ ላይ
ወርሃዊ ሪፖርት አዘገጃጀት	የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የክምችት ሁኔታ ሪፖርት	✓ በሪፖርት ጥራዝ ላይ	
	የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የገቢ ሪፖርት	✓ በሪፖርት ጥራዝ ላይ	

የሚከተሉት ሰነዶች በአንድ ላይ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡

- የአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ ወጪ ሠነዶችና የመረከቢያ ሠነዶች፡ በስርጭት ጣቢያ ገቢ የተደረጉ የእርዳታ ቁሳቁሶችን ብዛት ያመላክታሉ፡፡
- የዕቃ መጠየቂያ ወይም መልቀቂያ ሰነድ እና የስርጭት ጣቢያ የወጪ ሰነድ፡ በወረዳው አስፈላጊው ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ ከስርጭት ጣቢያ በተከታታይ የተሰራጩትን የእርዳታ ቁሳቁሶች ያመላክታሉ፡፡

ከላይ በተገለጸው ሰንጠረዥ መሰረት ሁሉም ቋሚ የስርጭት ጣቢያዎች የመሰረታዊ የእርዳታ ቁሳቁስ እንቅስቃሴ መዝግበው መያዝ አለባቸው፡፡ ቋሚ ላልሆኑ የስርጭት ጣቢያዎች ግን መረጃውን በወረዳ ጽ/ቤት ማስቀመጥ ይኖርባችኋል፡፡

---

* ከስርጭት ጣቢያ የእርዳታ ቁሳቁሶች እንዲወጡ ለማዘዝ እንደ ክልሉ አግባብ መሰረት የዕቃ መጠያቂያ ወይም የመልቀቂያ ትዕዛዝ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

አስገዳጅ የሥራ ሒደት ማጠናቀቂያ ቀናት

1st በማንኛውም የስርጭት ጣቢያዎች ባለፈው ወር ከአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የተረከባችሁት፣ ያከማቻችሁት ወይም ያከፋፈላችሁት የእርዳታ ቁሳቁሶችን ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን ሪፖርት ማዘገጃት ይኖርባችኋል፡፡ በወሩ መጀመሪያ ቀን ቆጠራ በማካሄድ የእያንዳንዱን ሪፖርት ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለባችሁ፡፡


ቆጠራ እንድታካሄዱና የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ ሪፖርት ለማዘጋጀት እንድትችሉ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ወር በገባ በመጀመሪያ ቀን ጠዋት ስርጭት ላይካሄድ ይችላል፡፡ ያልታሰበ ድንገተኛ አደጋ ካላጋጠመ በስተቀር በወሩ የመጀመሪያ ቀን አሽከርካሪው በስርጭት ጣቢያ ለማራገፍ ከተገኘ ወርሃዊ ቆጠራችሁን እና የስርጭት ጣቢያ ሪፖርት አዘጋጅታችሁ እስከምትጨርሱ ድረስ መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ ሪፖርቶች በተቻለ ፍጥነት ወር በገባ እስከ 10ኛው ቀን ድርስ ወረዳ ጽ/ቤት እንደሚደርስ ማረጋገጥ ይኖርባችኋል፡፡ **10ኛው**

21 ቀናት ከአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የእርዳታ ቁሳቁሶችን የጫነ ተሽከርካሪ በወረዳ ጣቢያ ለመድረስ የመጨረሻውን እርዳታ የጫነ ተሽከርካሪ የሚፈጅበት ከፍተኛው ቀን ነው፡፡ በነዚህ ቀናት ውስጥ ለወረዳው የተመደበው እርዳታ ተጠቃሎ ያልደረሰ ከሆነ የወረዳው ባለሙያዎች/ኤክስፐርቶች የክልሉን ሃላፊዎች ወዲያው አስቸኳይ ምርመራ እንዲካሄድ ያሳውቃሉ፡፡

7 ቀናት የእርዳታ ቁቁሶች (በዙር ወይም በወር የተመደቡ) በስርጭት ጣቢያው ገቢ ከተደረጉ በኃላ ለሁሉም ቀበሌዎች የእርዳታ ቁሳቁሶቹን ለማሰራጨት የሚፈጀው ከፍተኛ ቀን ነው፡፡ እንደ መጋዘን ሰራተኛነታችሁ በነዚህ ቀናቶች ውስጥ ከስርጭት ጣቢያ መጋዘን ለተፈቀደላቸው አከፋፋዮች የእርዳታ ቁሳቁሶቹን ለማስረከብ የእናንተ መገኘት አስፈላጊ ነው፡፡

የዕርዳታ ቁሳቁሱ ተጠናቅቆ እንደገባ ወረዳው ቀበሌዎቹን ያሳውቃል፡፡ ቁሳቁሶቹ ተጠናቀው እንደገቡ ቀደም ብሎ ወይም በ3ኛው ቀን ስርጭቱ መካሄድ መጀመር ሲኖርበት በተጨማሪም በተቀመጠው የ7 ቀናት ጊዜ ገደብ ውስጥ ስርጭቱን ለማጠናቀቅ ጠዋትና ከሰዓት በኋላ በማከፋፈል 10 ቀበሌዎች የሚገባቸውን እርዳታ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ የጊዜ ገደብ ተግባራዊ የማይሆነው ስርጭቱ ከ10 ቀበሌዎች በላይ ሲያቅፍ ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ቀበሌ ግማሽ የስርጭት ቀን ስለሚወሰድ ነው፡፡



ማሳሰቢያ - ቀናቱ የሚከተሉት የቀን መቁጠሪያን እንጂ የሰራ ቀናትን አይደለም፡፡

የእርዳታ ቁሳቁስ ብዛት ስሌት ሠንጠረዥ

የእርዳታ ቁሳቁሶችን ከቦታ ቦታ መዘዋወር ሪፖርት በምታደርጉበት ወቅት ከዚህ በታች የሚገኘውን የእርዳታ ቁሳቁስ ብዛት ስሌት ሰንጠረዥ መጠቀም ይኖርባችኋል፡፡ ማሳሰቢያ 1 ሊትር የምግብ ዘይት ከ1 ኪ.ግ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ይህም ማለት 100 ሊትር ዘይት ከ1 ኩንታል ጋር እኩል ነው፡፡

ሊትር (የምግብ ዘይት)	ኪሎ ግራም (ኪ.ግ)	ኩንታል
1	1	0.01
100	100	1

ክልካዊ ሰነዶች/ቅጾች


በክልሉ መንግስት የሚዘጋጁ የእርዳታ ቁሳቁሶችን ለመረከብና ለማሰራጨት የምትጠቀሙባቸው ክልላዊ ሰነዶች/ቅጾች ናቸዉ፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘረውን መመሪያ ማለትም እያንዳንዱን ቅጅ ለማን እንደምትሰጡ እንዲሁም በፎርሞቹ/ቅጾቹ ላይ የሚገኘውን የአጠቃቀም መመሪያ መከተል ይኖርባችኋል፡፡

የቅጅዎች ቀለም ሊለያይ ይችላል፡፡ አስፈላጊው ነገር የቅጅዎቹ ቁጥር/ብዛት ነው፡፡

ለአፋር ፣ ለአማራ ፣ ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ፣ ለጋምቤላ አና ለትግራይ ክልሎች የሚያገለግሉ ቅጾች/ፎርሞች




የእርዳታ ቁሳቁስ መረከቢያ ወቅት ፡-






የእርዳታ ቁሳቁስ ስርጭት ወቅት ፡-



ለሐረሪ ክልል




የእርዳታ ቁሳቁስ መረከቢያ ወቅት ፡-






የእርዳታ ቁሳቁስ ስርጭት ወቅት ፡-



ለድሬደዋ መስተዳደርና የደቡብ ክልል




የእርዳታ ቁሳቁስ መረከቢያ ወቅት ፡-






የእርዳታ ቁሳቁስ ስርጭት ወቅት ፡-



ለኦሮሚያ ክልል




የእርዳታ ቁሳቁስ መረከቢያ ወቅት ፡-





የእርዳታ ቁሳቁስ ስርጭት ወቅት ፡-



ከአሽከርካሪው የተቀበላችሁትን የአ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የወጪ ሰነድ ቅጅ በጥራዙ ላይ ከሚቀረው የመረከቢያ ሰነድ ጋር ማያያዝ ይኖርባችኋል ፡፡

ከወረዳው የተቀበላችሁትን የዕቃ መጠየቂያ ወይም የመልቀቂያ ሰነድ ቅጅ (ክልላችሁ የሚጠቀም ከሆነ) በጥራዙ ላይ ከሚቀረው የስርጭት ጣቢያ ወጪ ሰነድ ጋር ማያያዝ ይኖርባችኋል ፡፡

4

ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን የሚሰሩ ስራዎች ዝርዝር መቆጣጠሪያ (ቼክ ሊስት)

ባለፈው ወር ማንኛውንም አይነት የእርዳታ ቁሳቁስ ከተረከባችሁ ፣ ካከማቻችሁ ወይም ወጪ ካደረጋችሁ የሚከተሉትን ተግባራት እኢአ ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን ማከናወን ይኖርባችኋል፡፡

የቁሳቁስ ቆጠራ

ቆጠራ በማካሄድ ወርሃዊ የስርጭት ጣቢያ የክምችት ሁኔታ ሪፖርትና የስርጭት ጣቢያ መዝገብ/ሌጀር በመረጃው መሰረት በትክክል ሪፖርት እንደተደረጉ ማረጋገጥ ይኖርባችኋል፡፡

የስርጭት ጣቢያ መዝገብ/ሌጀር

ለሚቀጥለው ወር ከወጪ ቀሪውን (በወርሃዊ ቆጠራ) ካረጋገጣችሁ በኋላ በስርጭት ጣቢያ መዝገብ በእያንዳንዱ ገፅ ላይ መፈረም ይኖርባችኋል፡፡ በተጨማሪም ለእያንዳንዱ የዕርዳታ ቁሳቁስ አይነት በአዲስ ገፅ መጀመር/መጻፍ ይኖርባችኋል፡፡ ይህ አሰራር በቀላሉ የሚቀጥለውን ወር የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ ሪፖርት ለማዘጋጀት ይረዳችኋል፡፡

የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የገቢ ሪፖርት

በእያንዳንዱ ጊዜ የእርዳታ ቁሳቁሶች ገቢ በሚደረጉበት ወቅት ይህ ሪፖርት ደረጃ በደረጃ መጠናቀር ይኖርበታል፡፡ ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባችኋል፡-

- እያንዳንዱ ገቢ **በመረከቢያ ሰነድ** ቅጅ የተደገፈ መሆኑን ማረጋገጥ (በመረከቢያ ሰነድ ጥራዝ ላይ)
- **በስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የክምችት ሁኔታ ሪፖርትና በስርጭት ጣቢያ መዝገቡ** መረጃ መሰረት ገቢ የተደረጉት የዕርዳታ ቁሳቁሶች ድምር ከጠቅላላው ድምር ጋር እኩል መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡
- ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት መፈጸማችሁን እና ለወረዳው ሪፖርት በሶስት ቅጅ መላካቹህን ለማረጋገጥ በእያንዳንዱ የሪፖርት ገጽ ላይ መፈረም፡፡

የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የክምችት ሁኔታ ሪፖርት

ሪፖርቱን በማዘጋጀት የሚከተሉትን ማረጋገጥ ይኖርባችኋል፡-

- የዚህኛዉ ወር የስርጭት ጣቢያ የክምችት ሁኔታ ሪፖርት የወሩ መጀመሪያ ከወጪ ቀሪ ከባለፈዉ ወር ሪፖርት የወሩ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ ጋር እኩል መሆኑን አረጋግጡ፡፡
- ለእያንዳንዱ የቁሳቁስ ዓይነት እና የምደባ ዙር/ወር የሚከተሉትን አረጋግጡ፡-
  የወሩ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ = የወሩ መጀመሪያ ከወጪ ቀሪ + በወሩ ውስጥ ገቢ የተደረጉ - በወሩ ውስጥ የተሰራጩ - በወሩ ውስጥ የተበላሹ/የጠፉ
- በእያንዳንዱ የሪፖርት ገፅ ላይ በመፈረም አንድ ቅጅ ለወረዳው መላክ፡፡

መዝገብ አያያዝ

የሚከተሉት መረጃዎች በቀላሉ የሚገኙበት ሰፍራ መኖራቸውን ማረጋገጥ፡-

- **በመረከቢያ ሰነድ** ጥራዝ ላይ ቀሪ ከሆነው ቅጅ ጋር **የኢ/መ/ዝ/ም/ዋ/ዘ የወጪ ሰነድ መያያዙን**፣
- **በስርጭት ጣቢያ የወጪ ሰነድ** ጥራዝ ላይ ቀሪ ከሆነው ቅጅ ጋር **የዕቃ መጠየቂያና መልቀቂያ ሰነድ** መያያዙን፣
- እያንዳንዱ ሪፖርት ቅጅ በጥራዙ ላይ ቀሪ መደረጉን 1) **የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የገቢ ሪፖርት** 2)**የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ የክምችት ሁኔታ ሪፖርት**፡፡

ይህ ለምን አስፈላጊ ሆነ?

የእርዳታ ቁሳቁስ አስተዳደር፡ ቁሳቁሶችን በተቀላጠፈና በተገቢ ሁኔታ ለማስተዳደር እንዲቻል የኢትዮጵያ መንግስት በእያንዳንዱ መጋዘን የተከማቸውን የእርዳታ ቁሳቁሶችን መጠን/ብዛት በቂ መረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ ወርሃዊ ሪፖርቶች መንግስት ትክክለኛውን ውሳኔ እንዲያስተላልፍ መረጃ ይሰጣሉ፡፡ ያለ ስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ ሪፖርቶች የመንግስት ውሳኔዎች ይጨናገፋሉ ወይም አይተገበሩም፡፡

ለለጋሽ ድርጅቶች ሪፖርት ስለማድረግ፡ በልማታዊ ሴፍቲኔት እና በእለት ዕርዳታ ፕሮግራሞች በወረዳ ደረጃ ገቢ ተደርገው የሚሰራጩት አብዛኛው የእርዳታ ቁሳቁስ የተገኙት ከለጋሽ ድርጅቶች ነው፡፡ እያንዳንዱ ለጋሽ ድርጅት የዕርዳታ ቁሳቁሶቹን እንቅስቃሴ እና ለተጠቃሚው መድረሳቸውን የሚያረጋግጡ ወቅታዊና ትክክለኛ ሪፖርት ይፈልጋሉ፡፡ ይህ አሰራራር ባለፉት ጊዜያት በጣም አስቸጋሪ በመሆኑ በርካታ ለጋሽ ድርጅቶች የሚሰጡትን ድጋፍ ሲያቋርጡና ልገሳውን ላለመቀጠል ውሳኔዎችን ሲያደርጉ ነበር፡፡

የመንግስት ክፍያዎች፡ በስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ ሪፖርት መሰረት ለጋሽ ድርጅቶች ለቁሳቁሶች ማጓጓዣ፣ ለማከማቻ እና ለማሰራጫ ለመንግስት ክፍያዎችን ይፈፅማሉ፡፡ ይህም ስራዎችን ለማቀላጠፍ ይረዳል፡፡ ትክክለኛ እና ወቅታዊ የሆነ የስርጭት ጣቢያ ወርሃዊ ሪፖርቶች አለማቅረብ ግን የወደፊት ክፍያዎችን የሚያዘገይና በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራምና በዕለት እርዳታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል ወይም የፕሮግራሞቹ ስራ እንዲዘገዩ ያደርጋል፡፡